እየጨመረ ለመጣው የድርቅ አደጋ ምላሽ መስጠትና ከፍተኛ ተጋላጭ/ተጎጂ ለሆኑ ማህበረሰቦች ፆታን ያገናዘበ ከጉዳት ማገገሚያ መንገድ መገንባት

የአካባቢያዊና ማህበራዊ

አያያዝ/አጠቃቀም ዕቅድ

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ይህ አካባቢያዊና ማህበራዊ አያያዝ ዕቅድ የኢትዮጵያ መንግስት ለአረንጓዴ የአየር ንብረት ፈንድ የነደፈውን #እየጨመረ ለመጣው የድርቅ አደጋ ምላሽ መስጠት@ ከፍተኛ ተጋላጭ/ተጎጂ ለሆኑ ማህበረሰቦች ያታን ያገናዘበ ከጉዳት ማገገሚያ መንገድ መገንባት; የሚል ዕቅድ ለመደገፍ የተዘጋጀ ነው። ይህ ፕሮጀክት የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም(የተመልፕ) በጂ ሲ ኤፍ ባለው እውቅና እና ሚና መሰርት የሚደገፍ ሲሆን በ የተመልፕ ማህበራዊና አካባቢያዊ ደረጃዎች መመዘኛ መሰርት ተጣርቶ መካከለኛ ስጋት እንዳለው ታምኖበታል(አለም አቀፍ የገንዘብ ኮርፖሬሽን/አለም ባንክ ምድብ ለ ፕሮጀክት)።

የፕሮጀክቱ ዳራ

የፕሮጀክቱ አላማ በአየር ንብረት መዛባት ምክንያት ለከፋ ድርቅ ተጋላጭ ለሆኑ ማህበረሰቦች ከጉዳት ማገገሚያ መንገድ መገንባት ነው። ይህ ደግሞ በመሰረታዊነት አሁን ያለውን የገጠሩን ማህበረሰብ የግብርና ህይወት በተለያዩ የአየር ፀባዩን በተከተሉና ለወደፊት የሚመጣውንም የአየር ፀባይ ለውጥ የተላመዱ አሰራሮችን እንዲጠቀሙ ማስቻልን ይጠይቃል።

የቀረበው ዕቅድ መልከዓ ምድርን መሰረት ያደረገና በዘዴ የተገነባ ከድርቅ በማገገምና የዝናብን ተለዋዋጭነት ከራሳቸው ጋር በማስማማት ረገድ በኢትዮጵያ የገጠሩ ማህበረሰብ ላለበት ችግር ምላሽ ይሰጣል። አሁን ያለውን እውቀትና የወደፊት ትምህርት በመላው ኢትዮጵያ የተለያዩ ዝርፎችና ማህበረሰቦች መድረሱን ለማረጋገጥ ፕሮጀክቱ በአንድ ክልል ውስጥ ቢያንስ በአንድ ወረዳ በአጠቃላለይ በ 10 ክልሎች ውስጥ 22 ወረዳዎች ላይ (ስዕል 1) ተፈፃሚ በመሆን በድምሩ 2.5 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎችን(ስዕል 1) ተጠቃሚ ያደርጋሉ። ፕሮጀክቱ ሲቀረፅ በአንድ ወረዳ ውስጥ በአማካይ 8 ቀበሌዎች(ክፍለ-ወረዳ) ላይ ድጋፍ ተሰጥቶት ተፈፃሚ እንደሚሆን ታሳቢ አድርጓል። ወረዳዎቹ የተመረጡት በአየር ንብረት መዛባት ለሚከሰት ድርቅና የዝናብ ተለዋዋጭነት ያላቸውን ተጋላጭነትና ተጠቂነት መሰረት በማድረግ ነው። እንዲሁም ሌሎች ወሳኝ ነጥቦች በተለይ በአካባቢው ያለው በቂ ውሃ፣ የገበያ ቦታ ቅርበት/ተደራሽነት እና ማህበረሰቡና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በፕሮጀክቱ ለመሳተፍ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያገናዘበ ነው።

ስዕል 1፡ ፕሮጀክቱ የሚተገበርባቸው ቦታዎች



የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ
የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ሰንጠረዥ 1፡ ለፕሮጀክቱ የተለዩ ወረዳዎች

ክልል	የተመረጡ ወረዳዎች	የህዝብ ብዛት	
		ወንድ	ሴት
ትግራይ	ታህታይ ቆራሮ፣ ሳዕሲ ጻድአምባ	47,657	45,599
አማራ	እነብሴ ሳር ምድር፣ ታች ጋይንት፣ ላስታ	210,165	206፣186
ደ/ሕ	ማረቆ፣ ሃደሮ ቱኒቶ፣ ሃላባ	249,020	248,284
ኦሮሚያ	ቤሎ፣ ዝዋይ ዱግዳ፣ ጂዳ፣ መኢሶ	252,325	255,463
ጋምቤላ	አቦቦ፣ እታንግ	33,003	34,037
አፋር	ገዋኔ፣ ያሎ	18,551	21,951
ሶማሌ	ጂግጂጋ፣ ቀብሪ በያህ	258,975	288,903
ሃረሪ	ሃረሪ	115,000	117,000
ድሬዳዋ	ቢዮ አዋሌ	1,985	1,956
ቤንሻንጉል ጉሙዝ	ጉባ፣ ወምበራ	48,269	46,058
	ድምር	**1,234,860**	**1,265,467**

ፕሮጀክቱ 3 ዋና ዋና እና የተለያዩ ተግባራትን ያካተቱ ተጓዳኝ ንዑስ ክፍሎች/ይዘቶች አሉት።

1. **ለተጎጂዎች ኑሮ የቴክኖሎጂና የመሰረተ ልማት መፍትሄዎች፡-** የዚህ ክፍል ዋና አላማ የእርሻና ከብት እርባታ ምርታማነትን ማሳደግ እና ተስማሚውን ቴክኖሎጂ ያለማቋረጥ በማስተዋወቅ የመሬትን መጎዳት መቀነስ ነው። በተጨማሪም አጋዥ መሰረተ ልማቶችን በማስፋፋትና የድርቅን ዘርፈ ብዙ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን በመቀነስ ለተጋላጭ/ተጎጂ ማህበረሰቦች የተሻለ ከጉዳት የማገገም አቅም መፍጠር ነው።
2. **የተለያዩ መተዳደሪያዎችን መፍጠርና ጥበቃ ማድረግ፡-** ይህ ክፍል ተጎጂዎች ከፍተና ዋጋ ያላቸውን የግብርና ስራዎችን (ለምሳሌ፡ ዘመናዊ አትክልትና ፍራፍሬ ማምረት፣ ለግንባታ የማይሆኑ የደን ውጤቶች) እንዲያሳድጉ በመደገፍ የተለያ መተዳደሪያዎችን መፍጠር ሲሆን በተጨማሪም በግብርና እና በከብት እርባታ ውጠቴች መካከል ያለውን ጠቃሚ ቁርኝት ማጠናከር ነው።
3. **አካባቢን ማብቃት/ማጠናከር፡-** ተጋላጭ/ተጎጂ ማህበረሰቦች ከጉዳት እንዲያገግሙና በየደረጃው የሚጋጥሙ የአቅም ችግሮችን በለውጥና በማቋርጥ መንገድ ተደራሽ ለማድረግ አካባቢን ማጠናከር ወሳኝ ነው። ይህም የአየር ንብረትን ያገናዘበ፣ የተቀናጀ የማቀድና የበጀት አጠቃቀም መንገድ መዘርጋትን/ማጠናከርን፣ ተቋማዊ አቅምን ማሳደግንና ብቁ የሆነ የፕሮግራም አመራር ስልት መዘርጋትን ያካትታል።

ይህ ዕቅድ ሲዘጋጅ የታመነባቸው/የታሰቡ መነሻዎች

የሚከተሉት ነጥቦች ይህ ዕቅድ ሲዘጋጅ የታመነባቸው/የታሰቡ ናቸው።

ሀ. የትኛውም ትግበራ/ድጋፍ የሰዎችን ከአካባቢያቸው መፈናቀል አያስከትልም።

ለ. የትኛወም ትግበራ/ድጋፍ የተለየ ትኩረት/ጥንቃቄ የሚፈልጉ አካባቢዎች ላይ አይተገበርም።
ሐ. የመሸርሸር ተጽዕኖን ለመቀነስ የውሃ ማጠራቀምና የአፈር መሸርሸር መቆጣጠሪያ ግንባታዎች በበጋ/ደረቅ ወቅት ይከናወናሉ።
መ. በእያንዳንዱ የፕሮጀክቱ ደረጃ ላይ ተገቢው የአፈር መሸርሸርና የዝቃጭ ቁጥጥር ይደረጋል።
ሠ. በፕሮጀክቱ ምክንያት ምንም አይነት ብክለት ወይም ኬሚካል ልቀት አይኖርም።

ገዥ ህግና ደንቦች

ብሔራዊ የአካባቢና ማህበራዊ ህግ

ኢትዮጵያ ውስጥ የሚረደጉ የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ከዚህ በታች በተብራሩት ፖሊሲዎችና መርሆዎች ቁጥጥር ይደረግባቸዋል።

ሀ. ህገ መንግስት
ለ. የአካባቢ ፖሊሲ
ሐ. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ፡ አዋጅ ቁጥር 299/2002
መ. የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር፡ አዋጅ ቀጥር 300/2002
ሠ. የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር፡ አዋጅ ቁጥር 513/2007
ረ. የኢንዱስትሪ ብክለቶችን መከላከል - የሚንስትሮች ምክር ቤት ህግ፡ አዋጅ ቁጥር 159/2002
ሰ. የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር መመሪያ፡ ሐምሌ 2000
ሸ. የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ስርዓት መመሪያ፡ ህዳር 2003
ቀ. የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ መመሪያ (ረቂቅ)፡ ግንቦት 2004 እና
በ. አረንጓዴ ልማት ለአየር ንብረት ስትራቴጂ/ስልት
በተጨማሪም ፕሮጀክቱ በ የተመልፕ የሚተገበር በመሆኑ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ህግ ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ከፍተኛ ደረጃ አለም አቀፍ ህግ ስር ያሉ ግዴታዎችንም ያከበረ ነው።

ሀ. ሕገ-መንግሥት

የፕሮጀጀክቱ አካላት እና ውጤቶች ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አብዛኞቹ ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣሙ ናቸው።

የፕሮጀክቱ ብዙ ገጽታዎች የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 43 (4) ድንጋጌዎች ፡-

የልማት ዋና ዓላማ የዜጎችን እድገትና መሰረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት ይሆናል¡ በማለት የሚገልጸውን ያሟላሉ።

የፕሮጀክቱ ስራዎች ለምሳሌ አነስተኛ መስኖ፣ የውሃ ተፋሰስ ጥበቃ እርምጃዎች እና የውሃ አቅርቦት ፕሮጀክቶች ከዚህ ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ ጋር የሚጣጣሙ ናቸው። እንደ ደን፣ ማዕድን እና መስኖ ያሉት የተለያዩ ሥራዎች ፕሮጀክቱ የሚፈልገው መሬት የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40(3) ድንጋጌ ፡-

የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው።¡ በማለት የሚገልጸውን ያረጋግጣሉ።

የፕሮጀክቱ ሥራዎች እና ውጤቶቻቸው የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 41 (6) ድንጋጌ ፡-

መንግስት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፤ እንዲሁም በሚያካሂደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ወታል፤ ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል።¡ በማለት ከሚገልጸው ጋር የተጣጣሙ ናቸው።

በፕሮጀክቱ አራማጆች እስካሁን የተካሄዱት ምክክሮች ለሕዝብ ይፋ ለማድረግ እን ከተጎዱ ወገኖች ጋር ለመመካከር የኢኤስኤም መስፈርቶች የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 43(2) ድንጋጌ ፡-

ዜጎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማህበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሀሳባቸውን የመጠየቅ በመብት አላቸው ።¡ በማለት የሚገልጽውን ያሟላል።

አንቀጽ 92 መንግስት ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን በሚነድፈበትና በሚፈጽምበት ጊዜ አካባቢን የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለበት እና መንግስትና ዜጎች አካባቢን ለመጠበቅ የጋራ ኃላፊነት እንደተጣለባቸው የሚመለከት ነው።

በመጨረሻም ይህ ዕቅድ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 44(1) ድንጋጌ ፡-

ሁሉም ሰዎች ንጹህና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው።¡ የሚለውን ያሟላል።

ለ. የአካባቢ ፖሊሲ

የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ መጋቢት 27 ቀን 1989 ዓም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀ ሲሆን አስር ዘርፍ እና አስር የዘርፍ ቅንጅቶች ፖሊሲዎችን ይዟል። የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ እንደ ግብ የዘላቂ ልማት ህሳቤን ይዟል፤ የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ፡-

> የሁሉንም ኢትዮጵያውያን ጤና እና የህይወት ጥራት ማሻሻል እና ማሳደግ፤ የተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ እና ባህላዊ ሃብቶችን በጥሩ ሁኔታ በማስተዳደርና በመጠቀም ዘላቂ ማህበራዊና ኢኮኖሚዊ ልማትን ማሳደግ እንዲሁም የወደፊቱ ትውልድ የራሱን ፍላጎቶች የማሟላት እድሉን ሳይነካ/ሳይቀንስ የአሁኑን ትውልድ ፍላጎቶች ማሟላት በማለት ይገልጻል።

ከአሁኑ ፕሮጀክት ጋር አግባብነት ያላቸው የተወሰኑ የፖሊሲው ድንጋጌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፤

ሀ. ድርቅ በሚያጠቃቸውና ዝቅተኛ ዝናብ ባላቸው ቦታዎች የውሃ ጥበቃን ማስፋፋት፣ ይህም ከአካላዊ የአፈር ጥበቃ ጋር እኩል አስፈላጊ ሲሆን የሰብል ማምረትን አካቶ የበለጠ አስተማማኝ እና የጨመረ የስነ-ህይወታዊ ምርት ላላቸው አካባቢዎች የሚደረገው ነው።

ለ. በእርሻ ማሳ፣ በመኖሪያ ቤት አካባቢ እና በተሸረሸሩ እና/ወይም በሚሸረሸሩ ተዳፋት የመሬት አቀማመጦች የማገዶ እንጨት፣ የግንባታ ቁሳቁሶች የሚሆኑ ዛፎችን ክምችት ለመጨመር የደን ልማትን ማስፋፋትና ለእደ ጥበብ እና ለሌሎች የዛፍ ውጤቶች ይህንኑ መፈጸም

ሐ. በተራቆቱ አካባቢዎች የሁሉንም አሁን ያሉ የመስኖ እቅዶችን ሙሉ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ ዳሰሳዎችን ማካሄድና አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ አሉታዊ የአካባቢ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎች የማስተካከያ ፕሮግራሞችን መቅረጽ፤

መ. የህዝብ ምክክር የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ዋነኛ አካል መሆኑን ማረጋገጥና የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አሰራሮች ገለልተኛ የግምገማና የህዝብ አስተያየት ድንጋጌ ያላቸውና ይህም በውሳኔ ሰጪዎች የሚታይ መሆን አለበት።

ሠ. የደን ማዕድን ልማት ስትራቴጂዎች የደን ሃብት ልማትን፣ አስተዳደርና ጥበቃን ከመሬትና ውሃ ሃብት፣ ከኢነርጂ ሃብት፣ ከኢኮሲስተምና የዘረመል ሃብት እንዲሁም ከሰብል ማምረትና ከእንስሳት እርባታ ጋር የተዋሃዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ረ. የአካባቢና የሃብት ልማት እና አያያዝ ከፕሮጀክት ጽንሰ ሃሳብ እስከ እቅድ ማውጣት፣ ከአፈጻጸም እስከ ቁጥጥርና ግምገማ ያሉት ሁሉም ምዕራፎች በሃብት ተጠቃሚዎችና አስተዳዳሪዎች ውሳኔዎች ላይ ተመስርተው የተከናወኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

የቀድሞ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ብዙ መመሪያዎችን ያወጣ ሲሆን የሚከተሉትንም ያካትታል፡ - I. የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ መመሪያ ሰነድ (2000)፤ II. የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ መመሪያ ሥነ-ስረዓት (2003) እና III. የ2004 የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ የሚከተሉትን ዘርፎች አካቷል፡ - ሀ. መንገድና የባቡር ሃዲድ፣ ለ. የአሳ ምርቶች፣ ሐ. ደን፣ መ. ሃይድሮ ፓወር ምርት ማጓጓዝና ማሰራጨት፣ ሠ. የመስኖ ፕሮጀክቶች፣ ረ. እንስሳትና እርባታ የተራቆተ መሬት፣ ሰ. የመዓድንና ፔትሮሊየም ስራ ፕሮጀክቶች፣ ሸ. የውሃ አቅርቦትና ቀ. ዘላቂ የኢንደስትሪ ዞን/ሪል-ስቴት ልማት።

ሐ. አዋጅ ቁ. 299/2002 የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ

የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ዋና ዋናዎቹ የልማት ፕሮጀክቶች፣ ፕሮግራሞችና እቅዶችን ለመፈጸም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማን አስገዳጅ መስፈርት አድርጎታል። አዋጁ አካባቢ፣ በኢኮኖሚ፣ ባህላዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎችን ለማጣመርና ለማጣጣም መሳሪያ ሲሆን ይህም የውሳኔ መስጠተው ሂደቶች ዘላቂ ልማትን በሚያበረታታ ሁኔታ መሆኑን ከግምት ውስጥ እንዲገባ ያደርጋል። በዚሁ የአዋጅ ህግ ውስጥ ሪፖርት በማንና ለምን እንደሚዘጋጅ፣ ዘዴዎቹ እና ለማን እንደሚቀርብ ተገልጾአል። ህጉ ለሚከተሉት ግልጽ ትርጓሜና ፍቺዎችን ሰጥቷል፡-

ሀ. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የማዘጋጀትን አስፈላጊነት
ለ. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ፕሮጀክትን ለመፈጸም ኤምኤስኢ ሊከተላቸው የሚገባቸው አሰራሮች
ሐ. የአካባቢያዊ ተጽዕኖ ጥናቶች ጥልቀት፤
መ. የትኞቹ ፕሮጀክቶች ሙሉ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንደሚፈልጉ
ሠ. የትኞቹ ፕሮጀክቶች ከፊል ወይም ምንም አይነት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንደሚፈልጉ ወይም እንደማይፈልጉ እና
ረ. ሪፖርቱ ለማን እንደሚቀርብ

መመሪያ ቁጥር 1/2008፡ ይህ መመሪያ የወጣው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸውን ፕሮጀክቶች በሚዘረዝረው አዋጅ ቁ. 299/2002 መሰረት ፕሮጀክቶችን ለመወሰን ነው። በቀረበው ፕሮጀክት የቀረቡት ማናቸውም ስራዎች የተዘረዘሩ ሲሆን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ያስፈልጋል ተብሎ አይጠበቅም። ይህ የሚለወጥ ወይም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የመለየት አስፈላጊነት ካለ በአፈጻጸሙ አካልነት ሙሉ ግምገማ የሚካሄድ ይሆናል።

መ. አዋጅ ቁ. 300/2002 የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ከአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ህግ ጋር በተጨማሪነት የልማት እንቅስቃሴዎች ከመቋቋማቸው በፊት በአካባቢ ተጽዕኖዎች ግምት መውሰድ እንዳለባቸው የሚጠይቅ ሲሆን የብክለት ቁጥጥር አዋጁ እየተፈጸሙ ያሉ ስራዎች የጥራት ደረጃ ገደብ ለማስቀመጥ የብክለት ደረጃቸውን የሚቀንሱ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው። በመሆኑም ህጉ ካሉት ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱ እየተፈጸሙ ያሉ እንቅስቃሴዎችን በሃገሪቱ ደረጃዎች እና ደንቦች መሰረት መጣጣማቸውን በመፈተሽ (የአካባቢ ቁጥጥር በማድረግ) ማረጋገጥ ነው።

ሠ. አዋጅ ቁ. 513/2007 የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር

አዋጅ ቁ. 513/2007 የደረቅ ቆሻሻን ከፍተኛ ጉዳት ለመከላከልና ከዚሁ ደረቅ ቆሻሻ የሚገኙ ጥቅሞችን ለማሳደግ የማህበረሰቡን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ ያለመ ነው።

አዋጁ በከተማ አስተዳደሮች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ የድርጊት እቅዶችን ያስቀምጣል።

ረ. አዋጅ ቁ. 159/2008 የኢንደስትሪ ብክለትን መከላከል- የሚኒስትሮች ምክር ቤት ድንጋጌ

አዋጅ ቁ. 300/2002ን ተከትሎ የኢንደስትሪ ልማት ከአካባቢ ጥበቃ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማረጋገጥ የኢንደስትሪ ብክለትን ለመከላከል ደንብ የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተዘጋጅቶ ነበር። ይህ ደንብ (አዋጅ ቁ. 159/2008) ለብዙ የኢንደስትሪና የማዕድን ስራዎች አጠቃላይ የኢንደስትሪ ብክለት ደረጃዎችን አካቷል።

ሰ. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ መመሪያ፣ ሐምሌ 2000

የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ መመሪያ ሰነድ የሚከተሉትን የሚሸፍኑ መሰረታዊ መረጃዎችን ይደነግጋል፡-

ሀ. በኢትዮጵያ የአካባቢ ግምገማ እና አያያዝን፤
ለ. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሂደትን፤
ሐ. ደረጃዎችና መመሪያዎች እና
መ. በኢትዮጵያ የዘርፍ አካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጉዳዮች የሚከተሉትን ሸፍኖ፡- ግብርና፣ ኢንደስትሪ፣ ትራንሰፖርት፣ማዕድን፣ ግድቦች እና ማጠራቀሚያዎች፣ የቆዳ ማልፊያ፣ ጨርቃጨርቅ፣ ኃድሮፓወር ጄኔሬሽን፣ የመስኖ ፕሮጀክቶች እና የሰፈራ ፕሮጀክቶች።

መመሪያው የሚከተሉትን እዝሎችም ይዟል፡-

ሀ. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማን በሙሉ፣ በከፊል የሚፈልጉ ወይም የማይፈልጉ እንቅስቃሴዎች፤
ለ. የማመልከቻ ናሙና ፎርሞች፤ እና
ሐ. ለውሃ እና ዐየር ደረጃዎችን እና መመሪያዎችን፡፤

ሸ. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ስርዐት መመሪያ፣ ሕዳር 2003

መመሪያው በኢትዮጵያ ውስጥ የልማት ፕሮጀክቶችን ማጣሪያ፣ ክለሳ እና የመፍቀድ ሂደቶችን ይዘረዝራል እና የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ለማከናወን መስፈርቶችን ያስቀምጣል።

ከፕሮጀክቱ ጋር አግባብነት ያላቸውን ሙሉ ወይም የመጀመሪያ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚፈልጉትን እንቅስቃሴዎች በእዝል II፣ ሰንጠረዥ 1 እና 2 ይዘረዝራል። ሆኖም መመሪያ ቁጥር 1/2008 (ከላይቨ የተጠቀሰው) ይህን ዝርዝር አሻሽሎታል እና በዚህም የትኞቹም የቀረቡ እንቅስቃሴዎች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አያስፈልጋቸውም።

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ቀ. የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ መመሪያ (ረቂቅ)፣ ግንቦት 2004

መመሪያው በኢትዮጵያ ለቀረቡት ልማቶች ለአካባቢ አያያዝ ዕቅድ መመሪያ ዝግጅት አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች እና የአካባቢ አያያዝ ዕቅድን ለመፈጸም ተቋማዊ እቅዶችን ይዘረዝራል። ይህ ዕቅድ የመመሪውን መስፈርቶች ያከብራል።

በ. የአረንጓዴ ልማት ለአየር ንብረት ስትራቴጂ/ስልት

የአረንጓዴ ልማት ለአየር ንብረት ስትራቴጂ የኢትዮጵያን በማደግ ላይ ያል አረንጓዴ ልማት የሚደግፉ አራት ምሰሶዎች ላይ ያተኩራል።

ሀ. የግብርና እና የመሬት አጠቃቀም እርምጃዎችን ስሙም አድርጎ መውሰድ/ማጽደቅ፤
ለ. በደን ውስጥ የጂኤችጂ ክምችትን መጨመር ማለትም ደኖችን ለኢኮኖሚያዊ እና ስነ-ምህዳራዊ አገልግሎታቸው መጠበቅ እና ወደ ነበሩበት መመለስ፤
ሐ. ታዳሽ እና ንጹህ የኃይል ማመንጫ ማጎልበት፤ እና
መ. በኢንዱስትሪ፣ ትራንስፖርት፣ እና ሕንጻዎች አግባብነት ያላቸውን የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም

በአጠቃላይ ለፈጣን አፈጻጸም አራት ኢኒሼቲቮች፡- i) የኢትዮጵያን የኃይድሮፓወር አቅም ማወቅ፣ii) ከፍተኛ መጠን ያለቸው የተሻሻሉ የገጠር ማብሰያ ቴክኖሎጂዎች፣ iii) የእንስሳት የዕሴት ሰንሰለት የመሻሻል ብቃት፣ እና iv) ከደን ጭፍጨፋ እና መመናመን የሚወጡትን ልቀቶች መቀነስ ተመርጠዋል።

የብሔራዊ ፖሊሲዎችን እና ሕጎችን ከ ጂ ሲ ኤፍ ደረጃዎች ጋር ማጣጣም

የአፈጻጸም ደረጃ 1፡- የአካባቢ እና ማህበራዊ ስጋቶችን እና ተጽእኖዎችን መገምገም እና መያዝ

የኢትዮጵያ አካባቢ ፖሊሲ ፕሮጀክቱ ጥሩ የአካባቢ እና ማህበራዊ አፈጻጸም ለማሳካት የሚመሩትን የአካባቢ እና ማህበራዊ ግቦችን እና መርሖችን የሚያስቀምጥ ሲሆን የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 299/2002) ደግሞ የፕሮጀክቱን የአካባቢ እና ማህበራዊ ጉዳቶችን/ስጋቶችን እና ተጽእኖዎችን ያስቀምጣል።

ይህ ዕቅድ እንደአግባብነቱ በጂሲኤፍ የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ያካተተ ሲሆን እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታል፡- i) ፖሊሲ፣ ii) ጉዳቶችን/ስጋቶችን እና ተጽእኖዎችን መለየት፣ iii) የአስተዳደር ፕሮግራሞች፣ iv) ድርጅታዊ አቅምና ብቃት፣ v) የአደጋ ዝግጁነት እና ምላሽ፣ vi) የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና vii) ቁጥጥር እና ግምገማ

የአፈጻጸም ደረጃ 2፡- የሠራተኛ እና ሥራ ሁኔታዎች

የኢትዮጵያ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 377/1996) የቅጥር ሠራተኞችን መብት ይጠብቃል እና ከጂሲቼፍ አፈጻጸም ደረጃ 2 ጋር ተመሳሳይ ድንጋጌዎችን ይዟል። የአዋጁ ድንጋጌዎች ለምሳሌ አሰሪዎች የሰራተኞቻቸውን ሰብዓዊ ክብር የመጠበቅ ግዴታ፣ ለሥራ ደህንነት እና ጤና ለመጠበቅ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች፣ እና የአሰሪውን እና ሰራተኞችን ግዴታዎች በግልጽ ደንግጓል። ሴት ሰራተኞችን በጾታቸው ምክንያት በደመወዛቸው ላይ አድሎ ማድረግ፤ እና በሰራተኞች መካከል በብሔራቸው፣ ጾታቸው፣ የፖለቲካ አመለካከታቸው ወይም በሌላ ማንኛውም ምክንያት አድሎ ማድረግ ሕገ-ወጥ ነው። የፕሮጀክት ፈጻሚዎች እነዚህ ብሔራዊ ሕጎች እና የጂሲኤፍ የአፈጻጸም ደረጃዎች በሁሉም የፕሮጀክት ሳይቶች መፈጸማቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። አፈጻጸም ደረጃ 2 ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናትን አለመቅጠር ሲያዝ አዋጁ ከ14 ዓመት ዕድሜ በታች ያሉ ሰዎችን መቅጠር ይከለክላል¡። በብሔራዊ እና ዓለመአቀፍ መስፈርቶች

መካከል አለመጣጣሞች በሚኖሩበት ጊዜ የበለጠ ጠንካራ የሆነውን ደረጃ/መስፈርት ወስዶ ለራስ በሚመች መልኩ መጠቀም ይመከራል።

የአፈጻጸም ደረጃ 3፡- ሀብትን በአግባቡ መጠቀምና እና ብክነትን መከላከል

የኢትዮጵያ ብክነት ቁጥጥር አዋጅ እና ደረጃዎች (አዋጅ ቁጥር 300/2002)። አዋጁ፡-

አንዳንድ የማህበራዊ እና አኮኖሚያዊ የልማት ሥራዎች ጥረቶችን የምርት ተጻራሪ ሊያደርጉ የሚችሉ አካባቢያዊ ጉዳትን ሊያስከትሉ ይችላሉ¡ ብሎ በመግለጽ ጀምሮ፣ በተጨማሪም ብክነትን የማይፈልግ የማህበራዊ እና አኮኖሚያዊ ልማት ውጤቶችን ማስወገድ ወይም ካልተቻለ ደግሞ መቀነስ አሰፈላጊ ነው¡ በማለት ይገልጣል።

አዋጁ የቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ደረጃዎችን እና ቅጣቶችን የያዘ ሲሆን የአዋጁ ድንጋጌዎች ከጂሲኤፍ ያፈጻፀም ደረጃዎች ጋር ይጣጣማሉ ብሎ መደምደም ይቻላል።

የአፈጻጸም ደረጃ 4፡- የማህበረሰብ ጤና፣ ደህንነት እና ሰላም

የጤና፣ መድሐኒት፣ ጤና እንክባካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 661/2009)

አዋጅ ቁጥር 661/2009 ከፕሮጀክቱ ጋር አግባብነት ያላቸው ጠቃሚ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

ሀ. ጥራቱ ከጤና ባለስልጣን ካልተረጋገጠ በስተቀር የውሃ አቅርቦት አግልግሎትን ከምንጭ፣ ከጉድጓድ ወይም ከቧንቧ መስጠት ክልክል ነው፤
ለ. ማንኛውም አሰሪ ለሰራተኞቹ የስራ ላይ የጤና አገልግሎቶች ማቅረቡን ማረጋገጥ አለበት፤
ሐ. ከመጠን በላይ ድምጽ የሚያወጡ ማናቸውንም ማሽነሪዎች ወይም መሳሪያዎች መጠቀም የተከለከለ ነው፤ ወይም የድምፅ መቀነሻ መሳሪያ መግጠም አለበት። እና
መ. ማንኛውም ሰው ደረቅ፣ ፈሳሽ ወይም ማንኛውንም ሌላ ቆሻሻ አካባቢን በሚበክል ወይም የማህበረሰቡን ጤና በሚጎዳ መልኩ ማስወገድ የለበትም።

የአፈጻጸም ደረጃ 5፡- መሬት ማግኘት እና አስገዳጅ ሰፈራ

የኢትዮጵያ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 456/2005) የመሬት ይዞታን ለሕዝብ ጥቅሞች ስመውሰድ እና ስለ ካሳ ክፍያ የሚደነግገው፤ እና የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 456/2005) ጂሲኤፍ የአፈጻጸም ደረጃ 5 የያዛቸውን ድንጋጌዎች ይሸፍናል።

አዋጅ ቁጥር 456/2005 ከጂሲኤፍ የአፈጻጸም ደረጃ 5 ጋር የሚጣጣሙ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች አካቷል፡-

ሀ. ለህዝብ/መንግስት ጥቅም ከመሬት ይዞታው የሚፈናቀል ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ከሰራው ልማት ወይም ካፈራው ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ይሰጠዋል፤ ወይም በመሬቱ ምትክ ተስማሚ መሬት ይሰጠዋል፤

ለ. የተሸረሸሩ/የተቦረቦሩ የገጠር መሬቶች በግል ወይም በአካባቢው ባለይዞታዎች እና እንዳሰፈላጊነቱ በአካባቢው ማህበረሰብ የስነ-ህይወታዊ እና አካላዊ ሥራዎችን በመጠቀም እንዲያገግሙ ይደረጋሉ።

ለመንግስት/ህዝብ ጥቅም የገጠር የመሬት ይዞታን መውሰድ እና የካሳ ክፍያ አዋጅ ቁጥር 455/200፡-

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር በዚህ አዋጅ መሰረት በቅድሚያ ካሳ በመክፈል በመንግስት አካል፣ የግል ባለሀብቶች፣ የህብረት ሥራ ማህበራት ወይም ሌሎች አካላት የላቀ የልማት ፕሮጀክትን ለማከናወን አገልግሎት ላይ መዋል አለበት ብሎ ሲያምን ወይም እንዲህ ዓይነቱ መውረስ በከፍተኛ የክልል ወይም የፌዴራል አካል ሲወሰን የገጠር ወይም የከተማ የመሬት ይዞታን የመውሰድ/መውረስ ስልጣን አለው፡፡ በማለት ይደነግጋል፡፡

ሕጉ ለሕዝብ/መንግስት ጥቅም ስለሚደረግ የመሬት ይዞታን መውረስ፣ ካሳ ክፍያ፡ የመሬት ባለይዞታዎች መፈናቀል፣ የቅሬታ እና ይግባኝ ሥነ-ሥርዓቶችን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡

በዚህ ፕሮጀክት ምንም አይነት የሰፈራ ሃሳብ የለም፡፡

የአፈጻጸም ደረጃ 6፡- የብዝሐህይወት ጥበቃ እና ህይወት ያላቸው የተፈጥሮ ሀብቶች ዘላቂ አያያዝ

አዋጅ ቁጥር 381/2004፣ የብዝሐህይወት ጥበቃ ኢነስቲትዩት እና ምርምር ማቋቋሚያ አዋጅ ለብዝሐህይወት ጥበቃ ኢነስቲትዩት የኢ. ኤክስ-ሲቱ እና የአይ ኤን-ሲቱ የመጠበቂያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ የሀገሪቱን ብዝሐህይወት ጥበቃ ማረጋገጥ አለበት፤፤ የሚል ስልጣን ሰጥቶታል፡፡

አዋጅ ቁጥር 482/2006 የዘረ-መል ሀብት እና የማህበረሰብ እውቀት እና ማህበረሰብ መብቶችን ይዳስሳል፡፡ የአዋጁ ዓላማ የሀገሪቱን የብዝሐህይወት ሀብት ጥበቃ እና ቀጣይነነት ያለውን አጠቃቀም ለማሳደግ ከብዝሐህይወት ሀብት አጠቃቀም የሚገኙ ጥቅሞችን ሀገሪቱ እና ህዝቦቿ በፍትሃዊነት እና በእኩልነት መካፈላቸውን ለማረጋገጥ፤ ነው፡፡ ቀጣዮቹ ድንጋጌዎች የዘረ-መል ሀብት የማግኘት መብት ላይ ያተኩራሉ፡

የአፈጻጸም ደረጃ 7፡- የሀገሬው ሰዎች

የኢትዮጵያ ህዝቦች የሀገሬው ሰዎች እንደመሆናቸው በዚህ ረገድ ልዩ ብሄራዊ ሕግ የለም፡፡ በኢትዮጵያ አውዳዊ ሁኔታ ይህ አግባብነት ላይኖረው ይችላል፤ ሆኖም በተመረጡት የፕሮጀክት አካባቢዎች ላሉ ማናቸውም የገጠር ማህበረሰቦች ድንጋጌዎቹ አግባብነት ያላቸው ናቸው፡፡ የአፈጻጸም ደረጃ 7 ድንጋጌዎች ይህን እቅድ በአግባቡ በመፈጸም ሊመለሱ ይችላሉ፡፡

የአፈጻጸም ደረጃ 8፡- ባህላዊ ትውፊት

የኢትዮጵያ የባህላዊ ትውፊት ምርምር እና ጥበቃ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 209/2000) የኢትዮጵያ የባህላዊ ትውፊት ምርምር እና ጥበቃ ባለስልጣንን የሚያቋቁም ሲሆን ባለስልጣኑ የተሰጠው ስልጣንም፤-

የባህላዊ ትውፊትን ለመጠበቅ እና ለመቆጣጣር፡- በባህላዊ ትውፊት ላይ መረጃዎችን ይሰበስባል እና የትውፊቱን ባህሪ ያስቀምጣል፣ ደረጃወንም ይመድባል፤ በይዘት፣ በጥቅም እና በባህላዊ ትውፊት ላይ አስፈላጊውን ትምህርት እና ምክር ይሰጣል፡፡

አዋጁ #ማንም ሰው ፈቃድ ካላገኘ አስተቀር ህንፃና መንገድ መገንባት፣ ማንኛውንም አይነት ቁፋሮ ማካሄድ ወይም መሬትን የሚያውክ ማንኛውንም አይነት ስራ በተከለሉ አካባቢዎች ላይ መስራት እንደማይችል; በአፅዕኖት ይከለክላል፡፡

ይህ ፕሮጀክትም ከላይ እንደተገለፁት እይነት ስራዎችን በተከለሉ ቦታዎች ላይ ለመስራት ሃሳብ አያቀርብም፡፡

ማጠቃለያ - ለአካባቢያዊና ለማህበራዊ አያያዝ ዕቅዱ የሚያስፈልጉ ተቋማዊ እገዛዎች

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

የኢትዮጵያ የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚንስቴር እና የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ይህን ዕቅድ ለፕሮጀክቱ የሚጠቀሙበት ሲሆን እንዳስፈላጊነቱ ልዩ ለሆኑና ውስን ቦታዎች ለሚገኙ ንዑስ ክፍሎች የበለጠ እንዲታገዝ ይሆናል። ይህ ዕቅድ የአካባቢና ማህበረሰብ ጉዳዮች በፕሮጀክቱ ላይ ያላቸውን ፖለቲካዊ ስጋት ለይቶ አውጥቶ ስጋቶቹን የሚወጣበትና አሉታዊ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅእኖዎችን የሚቀንስበት መንገድ ቀይሷል። በተጨማሪም በከፋ ሁኔታ የተጎዱ ማህበረሰቦች በፍጥንት ከጉዳታቸው የሚያገግሙበትን የጉዳት ካሳ መንገድ ይጠቁማል።

የአካባቢና ደን ሚንስቴር የዕቅዱን ተፈፃሚነት የሚቆጣጠር ሲሆን የተመልጥ ደግሞ ከሚንስቴሩ በሚሰጠው ድጋፍ ዕቅዱ በቂና ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል። ተቆጣጣሪው መሃንዲስ በየጊዜው የስራ ተቋራጩ የሚዎስዳቸው ማሰተካከያዎች ውጤታማ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

የአካባቢያዊና ማህበራዊ አያያዝ ዕቅዱ አላማዎች

ይህ ዕቅድ በፕሮጀክቱ የሚከሰቱ አካባቢያዊና ማህበራዊ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ የሚረዳ የአስተዳደር መሳሪያና የማህበራዊና አስተዳደራዊ አላማዎች ማስፈፀሚያ ነው። እንዲሁም ስራ ተቋራጩ በአካባቢ ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ እና የመቆጣጠሪያ ስልት ለመቀየስ የሚጠቀምበት ነው።

የፕሮጀክቶቹ አካባቢያዊና ማህበራዊ አላማዎች፡-

ሀ. የኢትዮጵያ የገጠሩን ማህበረሰብ ምርታማነትንና መተዳደሪያን እንዲያሳድጉ፣ በተፈተሹ መንገዶች የአየር ንብረት ለውጥን እንዲላመዱና በተቀናጀ መልኩ የሚገጥሟቸውን ችግሮች ተደራሽ እንዲደርጉና እንዲፈቱ ነው።

ለ. ለተለዩ አካባቢዎች ውሃ አቅርቦትን ማሻሻልና የውሃና የአፈር ጥበቃ/አጠቃቀም ዘዴዎችን ማስተዋወቅ

ሐ. ምርታማነትን ለማሳደግ አስተዳደርን ማሻሻል፣ መስኖን፣ የምርጥ ዘር አቅርቦትን፣ የተሸለ የከብት እርባታንና የብዝሃ ሰብል ልምድን ማሳደግ

መ. የዱቤ ስርኣት ተደራሽነትን በማስፋፋት የተሸለ የግብርና ምርታማነትን ማምጣት

ሠ. አደገኛ ሁኔታዎች ከመከሰታቸው በፊት የማስጠንቀቂያ አሰጣጥ ስርዓት በመዘርጋት በቂ የትንቃቄ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ

ረ. ዕቅድ በማውጣት፣ ተከታታይ የሆነ የአካባቢ ልማትን በቁርጠኝነት በማሳደግ ጥሩ አሰራርን ማበረታታት

ሰ. የውሃ፣ የአየርና የመሬት ብክለትን መቀነስና መከላከል

ሸ. አገር በቀል የሆኑ የዕፅዋት፣ የእንስሳትና ሌሎች አስፈላጊ ስርዓተ-ምህዳሮችን መጠበቅ

ቀ. ለአካባቢ ጥበቃ የወጡ ህጎች፣ ደንቦችንና ስርዓቶችን ማክበር

በ. በውጤታማነታቸው የተመረጡ አካባቢን የሚጎዱ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ የሚረዱ ልምዶችን ለራስ በሚመች መልኩ መጠቀም

ተ. አካባቢ ላይ የሚደርሱ ተፅዕኖዎችን ለመለየት የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት እና

ቸ. አካባበቢያዊ ግዴታዎችን በተመለከተ ለሚንስቴር መስሪያቤቱና ለተመልጥ ሰራተኞችና ለስራ ተቋራጩ አጠቃላይ ማብራሪያ/ግንዛቤ መስጠት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

እቅዱ በየጊዜው በስራ ተቋራጩ፣ ከተመልፕ ሰራተኞችና ከሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በመማከር የሚታደስና በፕሮጀክቶቹ የተብራራ የዲዛይን ስራ ላይ የሚጨመር ነው።

የአጠቃላይ አስተዳደሩ መዋቅርና ሃላፊነት

የአካባቢና ደን ሚንስቴር አስፈፃሚ አካል እንደመሆኑ ለሌሎች ሚንስቴር መስሪያ ቤቶች ልዑክ ያቀርባል።

እንዲሁም በሌሎች የሚንስቴር መስሪያ ቤቶች በተለይም በግብርናና የተፈጥሮ ሃብት ሚንስቴር፣ በከብትና የዓሳ እርባታ ኢንዱስትሪ ሚንስቴር እና በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሃይል ሚንስቴር ይታገዛል።

እነዚህ የፌዴራል የሚንስቴር መስሪያ ቤቶች በቀድሞው የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በተሰጣቸው የስልጣን ክልላቸው ይህን እቅድ የሚያስፈፅም ልዑክ ይኖራቸዋል። ለማሳያነት በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሃይል ሚንስቴር የቀረበ መዋቅር ከዚህ ጋር ተያይዟል (እዝል 1)።

ይህ ዕቅድ የፕሮጀክቱን ትግበራ አሰራር የተከተለና በፌዴራል፣ በክልለልና በወረዳ ደረጃ ያሉ የስራ ሃላፊዎችን ያካተተ ነው። በሁሉም ተሳታፊ የሚንስቴር መስሪያ ቤቶች የአካባቢ ጉዳይ ክፍሎች ቢኖሩም ከአራቱም የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ክፍሎች ሰራተኞች ጋር የሚሰራ የፕሮጀክት የአካባቢ አስተዳደር ባለሙያዎች ልዑክ መሰየም ይመከራል። እነዚህ የአካባቢ አስተዳደር ባለሙያዎች በክልልና በወረዳም ተዋቅረው ይሰየማሉ። አዲስ ሰራተኛ መቅጠር በሚያስፈልግበት ቦታ ተቀጣሪዎች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እንዲወስዱ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት ቅጥር መካሄድ ይኖርበታል።



ማሳያ 2. የፕሮጀክት አተገባበር መዋቅርና ለአካባቢያዊ ቅንጅት ሚና የቀረበ ማሳያ

የተመልፕ እና የአካባቢና ደን ሚንስቴር ለስራ ተቋራጩ አካባቢያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚያማክርና አካባቢያዊና ማህበራዊ ቁጥጥርና ሪፖርት የሚያደርግ እስፔሻሊስት የማቅረብ ሃላፊነት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

አለባቸው። የስራ ተቋራጩ እቅዱን የማስፈፀም፣ የፕሮጀክቱን ግንባታ የማካሄድ፣ በፕሮጀክቱ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ አካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖዎችን የመከላከልና የመቀነስ ሃላፊነትና ተጠያቂነት ሲኖርበት የአካባቢና ደን ሚንስቴር ወይም ልዑኩ ደግሞ የተቋራጩን አፈፃፀም ይከታተላል።

አስተዳደር

የአካባቢና ደን ሚንስቴር ስራው በሚተገበርበት ወቅት ይህን ሰነድ የመከለስና ማሻሻያ የማድረግ ሃላፊነት አለበት። ይህ ሃላፊነትም ለአንድ ሰው ይሰጣል።

የሳይት ተቆጣጣሪው በየቀኑ የግንባታ ሳይቱን አካባቢያዊ ፍተሻ የማድረግ ሃላፊነት አለበት። የአካባቢና ደን ሚንስቴር ወይም ልዑኩ ደግሞ በወርሃዊ ቁጥጥር የአካባቢያዊ ፍተሻውን ያረጋግጣል።

የስራ ተቋራጩ እና/ወይም በዚህ ፕሮጀክት ላይ የሚሳተፉ ሰዎች አስተዳደራዊና አካባቢያዊ ክንውኖችን፣ የቀረቡ ቅሬታዎችንና የተወሰዱ እርምጃዎችን በትክክል የመመዝገብና የማስቀመጥ ሃላፊነት አለባቸው።

ስራ ተቋራጩ የእቅዱን ተፈፃሚነት የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት።

የአካባቢና ደን ሚንስቴር አስፈፃሚ አካል ስለሆነ የእቅዱን ተፈፃሚነትና ውጤታማነት በተቋራጩ የመከታተልና የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት።

ተቆጣጣሪ መሃንዲሱ ወይም የፕሮጀክት ሃላፊው የስራ ተቋራጩን የሚቆጣጠር ሲሆን የአካባቢና ደን ሚንስቴር ደግሞ አካባቢዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን የመቆጣጠር ሃላፊነት አለበት።

የሳይት ተቆጣጣሪ

የሳይት ተቆጣጣሪው የእቅዱን ተፈፃሚነት የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት@ እንዲሁም ለተመልጥ ሰራተኞች፣ ለአካባቢና ደን ሚንስቴር፣ ለመሃንዲሶችና ለአጠቃላይ የግንባታ ሳይቱ ሰራተኞች በፕሮጀክቱ ውጤታማ አካባቢያዊ አስተዳደር ዙሪያ ምክር/ግንዛቤ ይሰጣል። በተጨማሪም በአካባቢያዊ ግንዛቤ ላይ ለፕሮጀክቱ ሰራተኞች ተገቢውን ስልጠና ይሰጣል። የቅሬታ ማስተካከያ እርምጃ አፈፃፀም ሪፖርት በተመልጥ ተዘጋጅቶ በአካባቢና ደን ሚንስቴር ለግንባታ ተቋራጩ ይሰጣል። በግንባታ ጊዜና ከግንባታ በኋላ እንዳስፈላጊነቱ ገለልተኛ የአፈፃፀም ግምገማ ሊደረግ ይችላል።

አካባቢያዊ መርሆዎች/ደንቦች እና ሳይትና ተግባር ተኮር ዕቅዶች/አሰራሮች

አካባቢያዊ መርሆች/አሰራሮች ልዩ አካባቢያዊ ይዘቶች በምን የአስተዳደር አላማዎች እንደሚተገበሩ በዕሁፍ ያሳያሉ። እንዲሁም ለሁሉም የግንባታ ስራዎች የሚያስፈልጉ የሳይትና ድርጊት ተኮር ተግባራት ዝርዝሮችን ይይዛል። የሳይትና የተግባር ተኮር ስራዎች ዕቅዶችና አሰራሮች የሚገለፁ ሲሆን ከዚህ በፊት በአፍሪካ ልማት ባንክ፣ አይ ዩ ሲ ኤን እና አለም ባንክ ተሰርተው ውጤታማ የሆኑ ተመሳሳይ ፕሮጀክቶችን ልምድ ይወስዳል።

አካባቢያዊ ክስተቶችን/አጋጣሚዎችን ሪፖርት ማድረግ

ማንኛውም አጋጣሚ፣ በእቅዱ አፈፃፀም ሂደት ውስጥ ያልተካተቱትንም ጨምሮ፣ በአጋጣሚዎች መመዝገቢያ ላይ በአግባቡና በዝርዝር ሊመዘገቡ ይገባል። ንብረት የማውደም/የማበላሸት ወይም አካባቢዊ ጉዳት የማድረስ አቅም ያለው አጋጣሚ ከተከሰተ የሳይት ተቆጣጣሪው በተቻለ ፍጥነት ለአካባቢና ለደን ሚንስቴር ያሳውቅና ሚንስቴሩ ያፀደቀው የመፍትሄ ሃሳብ እስኪዎሰድ ድረስ ግንባታውን ያቋርጣል።

እለታዊና ሳምንታዊ የአካባቢ ፍተሻ መከታተያ ቅፅ

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

እለታዊ የአካባቢ ፍተሻ ቅፅ በእያንዳንዱ ሳይት በየራሱ የሳይት ተቆጣጣሪ የሚሞላና በአግባቡ ተመዝግቦ ለአካባቢና ደን ሚንስቴር ተሰጥቶ የሚገመገም ይሆናል። ሳምንታዊ ቅፅ ደግሞ ያጋጠሙ ጉዳዮችንና የተሞሉ ዕለታዊ ቅፆችን አጠቃሎ በሳይት ተቆጣጣሪው ይሞላል።

ማስተካከያ እርምጃዎች

የአካባቢና ማህበራዊ አያያዝ ዕቅዱን የማያግዙ/የማይጣጣሙ ሁኔታዎች በሳምንታዊ የአካባቢ ፍተሻ ቅፅ መገለፅና መመዝገብ ይኖርባቸዋል። እንደጉዳዩ ክብደት የሳይት ተቆጣጣሪው በሳምንታዊው የሳይት ፍተሻ ሪፖርት ላይ የማስተካከያ እርምጃ ሊያስቀምጥ ይችላል። የሁሉም የማስተካከል እርምጃዎች ሂደት በመዝገብ ላይ ክትትል ሚደረግበት ሲሆን ማንኛውም ጉዳይና የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች ለአካባቢና ደን ሚንስቴር መቅረብና መማከር አለባቸው።

ግምገማና ቁጥጥር

ይህ ዕቅድና የአሰራር ሂደቱ በተመልጥ ሰራተኞችና በአካባቢና ደን ሚንስቴር በየሁለት ወሩ ይገመገማል። የግምገማው አላማ ይህን ሰነድ ለማሻሻል፣ በግንባታ ወቅት የተገኙ ልምዶችን ለማስገንዘብ፣ አዳዲስ እውቀቶችን ለማስጨበጥና የተቀየሩ የማህበረሰብ እሴቶችን ለማሳወቅ ነው። ማንኛውም ለውጥ ሲደረግ የተመልጥ እና የአካባቢና ደን ሚንስቴርን በማማከር ነው። ምንም አይነት ለውጥ ሲኖርም ሁሉም የሳይቱ ሰራተኞች በተቻለ ፍጥነት በስብሰባ እንዲያውቁት መደረግ አለበት።

የስራ ተቋራጮች ስልጠና

ዋናው ተቋራጭ አግባብ ያላቸው ባለሙያዎች፣ ተቋራጮችና ንዑስ ተቋራጮች እቅዱን፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ጉዳዮችንና ሃላፊነቶችን በሚገባ በማስገንዘብ ትክክለና አሰራር መዘርጋቱን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት። ሁሉም የግንባታው ሰራተኞች ጤናን፣ ደህንነትን፣ አካባቢያዊና ባህላዊ ፍላጎቶችን የሚያካትት ስልጠና ይወስዳሉ።

በማንኛውም አካባቢ ላይ ጉዳት ሊያስከትል በሚችል (ለምሳሌ፡- አደገኛ መሳሪያዎችን ማንቀሳቀስ) ስራ ላይ የተሰማሩ ሁሉም ሰራተኞችና የስራ ተቋራጮች ልዩ አካባቢና ተግባር ላይ ያተኮረ ስልጠና ይወስዳሉ።

ህዝብን ማማከር፣ እና አካባቢያዊና ማህበራዊ ግልጽኝነት

የአከባቢና ማህበራዊ አያያዝ ዕቅዱ ህዝብን ማማከር አንዱ የሚመለከታቸው አካላት የተሳትፎ ዕቅድ ክፍል በማድረግ አካቶታል። ፕሮጀክቱ ከአካባቢና ደን ሚንስቴር ሰራተኞች ጋር ተዘጋጅቶ በመንግስት የፀደቀ ነው። እስከታች ድረስ የወረደ የማማከር ስራ በፕሮጀክት ቀረፃው ወቅት የተተገበረ ሲሆን ከተጎጂ ማህበረሰቦች ጋር የሚደረገው ማማከር ሂደት እንደሚቀጥል ይጠበቃል። በህብረተሰቡ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ፕሮጀክት በህብረተሰቡ ሙሉ ለሙሉ ተቀባይነት እንደሚያገኝ ይታሰባል።

የተመልጥ እና የአካባቢና ደን ሚንስቴር በራሪ ወረቀቶችን በመደበኛነት በማዘጋጀትና በማሰራጨት ፍላጎቱ ላላቸውና ለሚመለከታቸው አካላት የፕሮጀክቱንና የግንባታውን ደረጃ ያሳውቃሉ። በሁሉም የፕሮጀክቱ ግንባታ ሳይቶች ለህዝብ ይፋ የሚደረግ የስልክ ቁጥር ይዘጋጅና ጥያቄዎችን፣ ጥቆማዎችንና ቅሬታዎችን ይቀበላሉ። ሁሉም ጥያቄዎች፣ ቅሬታዎችና ጥቆማዎች በሚገባ ተመዝግበው አግባብ ላለው የስራ ሃላፊ ይቀርባሉ።

ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ሲነሱ የሚከተሉት ነጥቦች ይመዘገባሉ፡-

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ሀ. የጥያቄዎች፣ ቅሬታዎችና ጥቆማዎች ሰዓት፣ ቀንና ባህሪይ/ዓይነት

ለ. የቀረበበት መንገድ (ለምሳሌ፡ በስልክ፣ በደብዳቤ፣ በአካል)

ሐ. ከጥያቄዎች፣ ቅሬታዎችና ጥቆማዎች በኋላ የተደረጉ ምርመራዎችና የተሰጡ መልሶች

ሠ. የተወሰዱ እርምጃዎችና እርምጃዎችን የወሰደው ሰው ስም

አንዳንድ ጥያቄዎች፣ ቅሬታዎችና ጥቆማዎችን ለመመለስ ርዥም ጊዜ ሊወስድ ይችላል ቢሆንም ለቅሬታ አቅራቢው ጉዳዩ የማጣራት ሂደት ላይ እንዳለ ሊነገረው ይገባል። ሁሉም ጥያቄዎች፣ ቅሬታዎችና ጥቆማዎች ተጣርተውና ውሳኔ ተሰጥቶባቸው በጊዜ አግባብ ለቅሬታ አቅራቢው ምላሽ መሰጠት አለበት። ይህ እቅድ በፍጥነት ሊፈቱ ለማይችሉ ጉዳዮች የጉዳት ካሳ አሰራርንም አካቷል።

የተመረጠው የስራ ተቋራጭ ሰራተኞች የሚቀርቡትን ጥያቄዎች፣ ቅሬታዎችና ጥቆማዎች የመገምገምና የመፍትሄ አሰጣጡን ሂደት የማረጋገጥ ሃለፊነት አለባቸው።

የቅሬታ ምዝገባና የጉዳት ካሳ አሰራር

በፕሮጀክቶች ግንባታና ትግበራ ምክንያት አንድ ግለሰብ ወይም የህብረተሰብ ክፍሎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አሉታዊ ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላል። ቅሬታዎች/ጉዳቶች የማህበራዊ ጉዳዮች ማለትም ከምልመላ መስፈርቶችና ከመብት ይገባኛል ጥያቄዎች፣ ከአገልግሎት መቋረጥ፣ ከጊዜያዊ ወይም ቋሚ መተዳደሪያን ማጣት እና ከሌሎችም ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች ጋር ሊያያዝ ይችላል። ቅሬታዎች/ጉዳቶች ከአካባቢ ጉዳዮች ማለትም ከመጠን ያለፈ ቆሻሻ/አቧራ መፈጠር፣ ከግንባታ ጥሬ እቃዎች ማጓጓዝ ብዛትና ንዝረት የተነሳ የመሰረተ ልማቶች መጎዳት፣ ከፍተኛ ድምጽ/ጫጫታ፣ የእንቅስቃሴ መብዛት፣ በመስኖና በመልሶ ማቋቋም ስራ ጊዜ የግል/የህዝብ የገፀ/ከርሰ ምድር ውሃ መጠን ወይም ጥራት መቀነስ፣ ከገቢ ወይም ከእርሻ መሬቶች ጉዳት ወዘተ ጋርም ሊያያዝ ይችላል።

እንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ሲከነሱ ቅሬታ አቅራቢዎች ከፕሮጀክቱ ሰራተኞች ጋር ልባዊ በሆነ አርኪ፣ ከአድሎ የፀዳ፣ ግልፅ፣ በጊዜ የተገደበና ወጭን በቀነሰ መንገድ ሊፈቱ ይገባል። ይህን ከግብ ለማድረስ ይህ እቅድ ለፕሮጀክቱ የጉዳት ካሳ አሰራር መንገድን አካቷል።

ፕሮጀክቱ ቅሬታ ያላቸው ወይም በፕጀክቱ ጉዳት ደርሶብናል የሚሉ አካላት ተገቢ በሆነ ሂደት ጉዳያቸውን እንዲያቀርቡ ይፈቅዳል። የቅረታዎች ምዝገባና የጉዳት ካሳ አሰራር ሂደቱ በዚህ እቅድ ላ በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን የፕሮጀክቱ አካል ሆኖ ለባለጉዳዮች በተለይም ወደ መደበኛ የህግ ተቋማት ለመሄድ ሰፊ እድል ለሌላቸውና ፈጣን እርዳታ ለሚፈልጉተጎጂዎች ተደራሽ፣ ፈጣንና ውጤታማ ምላሽ ለመስጠት ይረዳል።

ብዙ ቅሬታዎች ወዲያውኑ ሊፈቱ እንደሚችሉ ታሳቢ ብናደርግም እሂህ እቅድ ላይ የተገለፀው የቅሬታ ምዝገባና የጉዳት ካሳ አሰራር ሁለቱንም ወገን ያስማማ ፈጣን መፍትሄ ለመስጠት ይረዳል። ይህ የቅሬታ ምዝገባና የጉዳት ካሳ አሰራር ተቀረፀው፡-

ሀ. ህጋዊ አሰራር በመዘርጋት በባለድርሻ አካላት መካከል መተማመንን ለመገንባትና ትያቄያቸው ሚዛናዊ በሆነና ግልጽነት በተሞላበት መንገድ እታ እንደሆነ እንዲረጋግጡ

ለ. ችግሮቻቸውን ለማቅረብ እንቅፋት የገጠማቸው ቅሬታ አቅራቢዎች ካሉ ያልተወሳሰበና ግልጽ አሰራር በመዘርጋት በቂ እገዛ እንዲገኙ ለመርዳት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ሐ. በግልጽ የሚታይና ሚታወቅ አሰራር በመዘርጋት ለቅሬታ አቅራቢዎችም ሆነ ለሚመለከታቸው አካላት ምን አይነት ውጤቶች እንዳሉ በግልጽ ለማሳየት

መ. ለተጎጂዎች ያላሰለሰ፣ ቋሚ/የማይቀየር አቀራረብ፣ ሚዛናዊና ባለጉዳዮችን ያከበረ ትክክለኛና ተገቢ አያያዝ/እንክብካቤ መሰጠቱን ለማረጋገጥ

ሠ. ግልፀኝነት የተሞላበት ያቀረቡትን ቅሬታ ሂደት የሚያሳውቅ፣ በጉዳያቸው ምርመራ ሂደት የተገኙትን መረጃዎችና የመፍትሄውን ሂደት ተደራሽ ለማድረግ እና

ረ. ተከታታይ ትምህርቶችን በመስጠትና የጉዳት ካሳ አሰራሩን በተከታታይ ምዘና በማሻሻል የጎላ ቅሬታና የከፋ ጉዳትን ለመቀነስ ነው።

ለጉዳት ካሳ አሰራሩ የምልመላ/የመረጣ መስፈርቱ የሚያጠቃልላቸው፡-

ሀ. በግለሰብ/በቡድን ላይ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና አካባቢያዊ አሉታዊ ተፅዕኖ ደርሶ ሲታይ ወይም ሊያደርስ የሚችል ተጨባጭ ተፅዕኖ ሲኖር

ለ. በግልጽ ተለይቶ የተቀመጠ የደረሰ ወይም ሊደርስ የሚችል ተፅዕኖ ሲኖርና ፕሮጀክቱ ለጉዳቱ መድረስ ምክንያት የሚሆንበት ትንታኔ ሲቀርብ

ሐ. ጉዳት/ቅሬታ አቅራቢው ግለሰብ ወይም ቡድን በአካል ሲቀርብ ወይም ህጋዊ ወኪል ሲቀርብ

የአካባቢው ነዋሪዎች ወይም ሌሎች አካላት ሁሌም ለቀበሌ፣ ለወረዳና ለክልል መስተዳድሮች ቅሬታ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ስለዚህ ለማህበረሰቡ ስለ ፕሮጀክቱ ጠቀሜታና ስለ ጉዳት ካሳ አሰጣጥ ስርዓቱ ሊገነዘቡ ይገባል። የቀበሌ፣ የወረዳ እና የክልል ለዚህ ተብለው የተለዩ የአካባቢ ባለሙያዎች አድራሻ ለህዝብ ክፍት መሆን አለበት።

የቅሬታ አቅራቢዎች መዝገብ

ይህ የቅሬታ አቅራቢዎች መዝገብ የሚዘጋጀው በህብረተሰቡ የተነሱ ማናቸውንም ጉዳዮች መዝግቦ ለማስቀመጥ ነው። ማንኛውም ቅሬታ በቀረበ በ24 ሰዓት ውስጥ ለተመልጥ እና ለአካባቢና ደን ሚንስቴር መገለፅ አለበት። ቅሬታዎች በደንብ ከተለዩ በኋላ ከሙስናና ከብልሹ አሰራር ጋር ተያያዙ ጉዳዮች ወደ የተመልጥ ተልከው ውሳኔ ይሰጥባቸዋል ወይም ከኢትዮጵያ እንባ ጠባቂ ተቋም ጋር ምክክር ይደረግባቸዋል።

የቀረቡ ቅሬታዎችና የተስተናገዱበት መንገድ ጠቅላላ ዝርዝር በየ6 ወሩ በሚታተም ሪፖርት ላይ መውጣት አለበት።

የጉዳት ካሳ አሰራር

የጉዳት ካሳ አሰራሩ በመልካም ፈቃድና ጥረት ላይ የተመሰረተና ችግር ፈቺ እንዲሆን ተደርጎ የተቀረፀ ነው። ይህ አሰራር ህጋዊውን ሂደት እንዲተካ የታሰበ አይደለም። የጉዳት ካሳ አሰራሩ ተግባራዊ መሆን እስከሚችልበት ድረስ ቅሬታዎችን ወይም ጉዳቶችን ሁለቱም ወገኖች በሚስማሙበት መንገድ ለመፍታት ይሞከራል። በሂደቱ ጊዜ ሁሉም አካል በሁሉም ጊዜ በቅን ልቦና የሚሰሩ ሲሆን ሁለቱም የተስማሙበትን መፍትሄ የሚያዘገይ ወይም የሚያደናቅፍ ድርጊት ሊፈጽሙ አይገባም።

የእንባ ጠባቂ ተቋም ተጠሪነቱ ለፌደራሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆነ ፌዴራላዊ አካል ሲሆን በህገ-መንግስቱ ላይ የተቀመጡት የዜጎች መብቶች በህግ አስፈፃሚ አካላት አለመጣሳቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት

አለበት። ከተበላሸ አስተዳደር ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችን ተቀብሎ ይመረምራል፣ ህግን ተከተለ አሰራር መኖሩን ይከታተላል፣ እንዲሁም ለአስተዳደር በደሎች መፍትሄ ይሰታል/ይፈልጋል።

የክልል የህዝብ ቅሬታ ሰሚ ቢሮዎች ክልላዊ ተቋማት ሲሆኑ ተጠሪነታቸውም ለየክልሎቻቸው ፕሬዚዳንቶች ነው። ቢሮው ከህዝብ አገልግሎትና ከመልካም አስተዳደር ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችንና ይግባኞችን በመቀበል፣ በመመርመርና ማሳሰቢያ/ውሳኔ በመስጠት የመካስ ሃላፊነት አለበት። አብዛኞቹ ክልሎች ይህ የቅሬታ ሰሚ ቢሮ ሲኖራቸው ለየራሳቸው ዋና አስተዳዳሪዎች ተጠሪ ሆኑ ዞነ፣ የወረዳና የቀበሌ ቅርንጫፎችንም ዘርግተዋል። በቀበሌ ደረጃ ለተዋቀረው ቀበሌው አስተዳዳሪ ወሳኝ ነው።

አንድ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን በቅርቡ ላለ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ቅርንጫፍ ወይም ለአካባቢው የህዝብ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ በአካል በመገኘት ወይም በወኪሉ በቃል፣ በፁሁፍ፣ በፋክስ፣ በስልክ ዌም በሌላ መንገድ የማቅረብ አማራጮች አሉት። ቅሬታዎች/ጉዳቶች ይጣራሉ፣ ይመረመራሉ ከዚያም የመፍትሄ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል። በውሳኔው ያልረካ ቅሬታ አቅራቢ ጉዳዩን ወደሚቀጥለው ከፍ ያለ ደረጃ ወስዶ ይግባኝ ማለት ይችላል። በተጨማሪም አንዳንድ ክልሎች በወረዳ ደረጃ ተዘዋዋሪ የቅሬታ ሰሚ ቡድኖች አሏቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ባሉ ቢሮዎች ያልተፈቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት ኮማንድ ፖስቶችን አቋቁመዋል። የአካባቢና ደን ሚንስቴር መጠነ ሰፊ በፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች የተነሳ የሚከሰቱ አካባቢያዊና ማህበራዊ ጉዳቶች ቅሬታዎችን የሚቀበልበትና የሚያስተናግድበት አሰራር አለው። በሚንስቴሩ ውስጥ ቅሬታ/ጉዳት ሰሚ ተብለው የተሰየሙ ቅሬታዎችን አጣርተው ለመፍትሄው ከእንባ ጠባቂ ተቋም ጋር የሚሰሩ ሰዎች አሉት።

የማህበረሰቡ አባላት በፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች ምክንያት የተከሰቱ የአካባቢና የማህበራዊ ችግሮችን/ጉዳቶችን ለአረንጓዴ ልማት ለአየር ንብረት ስትራቴጂ/ስልት በተዘረጉት የሬድዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች በቅሬታ የማቅረብ መብት እንዳላቸው ይነገራቸዋል። የአረንጓዴ ልማት ለአየር ንብረት ስትራቴጂ/ስልት ፋሲሊቲ ድረ-ገፅ የህብረተሰቡን አደጋ መከላከል፣ ቅሬታን የማቅረብ መብትና የሚያቀርብበትን መንገድ የሚያሳይ መረጃን ያጠቃልላል።

ደረጃ	ሃላፊነት ያለበት ተቋም	አሰራር/ሂደት
በፌደራል ደረጃ	የአካባቢና ደን ሚንስቴርና የፕሮጀክቱ አስፈፃሚ ኮሚቴ	ሚንስቴሩ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል
	የፌደራል እንባ ጠባቂ	ጉዳዩ ወደ ፌዴራል ፍርድ ቤት ከመሄዱ በፊት የፌዴራል እንባ ጠባቂ ተቋም ላልተፈቱ ችግሮች

		ምክር መስጠት ይችላል
	የፌዴራል ፍርድ ቤት	በጉዳት ካሳ አሰራሩ ያልረኩ አመልካቾች ጉዳያቸውን ለመደበኛው የፍትህ ስርዓት ማቅረብ ይችላሉ።
በክልል ደረጃ	የክልል የአካባቢ ቢሮ እና ፒ ሲ ዩ	አመልካቾች ካልረኩ ወይም ወደ ክልል የአካባቢ ቢሮ ከተላኩ፣ ቢሮው በ 15 ቀን ውስጥ ምላሽ ይሰጣል
	የክልል እንባ ጠባቂ ቢሮ	አመልካቾች ከክልል እንባ ጠባቂ ቢሮም ምክር ማግኘት ይችላሉ
	የክልል ፍርድ ቤት	በአካባቢ ቢሮው ችግሩ ካልተፈታ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላሉ
በወረዳ ደረጃ	የወረዳ የአካባቢ ቢሮ	ቅሬታዎች ለወረዳ ከቀረቡ በ10 ቀን ውስት ምላሽ ይሰጣል። በወረዳው ምላሽ ካልረኩ ለክልል ፒ ሲ ዩ ወይም ለወረዳ መደበኛ ፍርድ ቤት ማመልከት ይችላሉ
	የወረዳ የእንባ ጠባቂ ቢሮ	አመልካቾች ከወረዳ እንባ ጠባቂ ቢሮም ምክር ማግኘት ይችላሉ
	የወረዳ ፍርድ ቤት	አመልካቾች ለመደበኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላሉ
በቀበሌ ደረጃ	የቀበሌ ሽንጎ	የቀበሌው ማህበረሰብ ወይም ሌላ የሚመለከተው አካል በፕሮጀክቱ ምክንያት ጉዳት መድረሱን ለቀበሌው አስተዳዳሪ ቅሬታ ማቅረብ ይችላል። ቀበሌውም በ10 ቀን ውስጥ ምላሽ ይሰጣል

እያንዳንዱ ወረዳ በአማካይ 100,000 ህዝብ ይኖርበታል። ቀበሌ የመንግስት ትንሹ የአስተዳደር መዋቅር ሲሆን በአማካይ 5,000 ሰዎች ይይዛል።

ከሙስናና ከማንኛውም ህገ-ወጥ አሰራር ጋር የተያያዘ ቅሬታ ወዲያውኑ ወደ ኢትዮጵያ እንባ ጠባቂ ተቋምና ኒው ዮርክ በተ.መ.ል.ፕ ስር ለሚገኘው የማጣራትና የምርመራ ቢሮ ይላካል።

በፕሮጀክት ደረጃ ካለው የጉዳት ካሳ አሰራር በተጨማሪ ቅሬታ አቅራቢዎች ለቅሬታም ሆነ ለካሳ የተመልጥ የተጠያቂነት አሰራር የመጠቀም እድል አላቸው። የማህበራዊና አካባቢያዊ ቅሬታ ሰሚ ክፍል የተመልጥ የደረጃዎች ማጣራት ሂደት ወይም በበቂ ሁኔታ ባልተተገበሩ ማህበራዊና አካባቢያዊ ስራዎች ምክንያት በሰው ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት ያስከተሉ ችግሮች ክሶችን ይመረምራል። ይህ የማህበራዊና አካባቢያዊ ቅሬታ ሰሚ ክፍል በማጣራትና ምርመራ ቢሮ ውስጥ ያለ ሲሆን በዋናው የቅሬታ ቢሮው ሃላፊ ይመራል። ለሁሉም ማህበረሰብና የተመልጥ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ያላቸው ተፅዕኖ ለሚመለከተው ግለሰብም ሆነ ማህበረሰብ

የቅሬታዎች ግምገማ እንዲቀርብ ይደረጋል። የማህበራዊና አካባቢያዊ ቅሬታ ሰሚ ቡድን ያለ ተፅዕኖ እና ያለ መድሎ የተጎጂዎችን ጥያቄ የመመርመርና ውጤቱንና የመፍትሄ ሃሳቡን ለህዝብ የማቅረብ ሃላፊነት ተሰጥቶታል።

የሚመለከታቸው አካላት ምላሽ አሰራር አመልካቾች/ተጎጂዎች በጋራ ተመካክረው በ የተመልፕ ፕሮጀክት ምክኒያት የተፈጠሩ አካባቢያዊና ማህበራዊ ጉዳታቸውን የመፍታት ዕድል ይሰጣቸዋል። ይህ አሰራር አመልካቾች የተመልፕ በአተገባበር ሂደቱ ላይ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ለሙሉ ፕሮጀክቱ አጋዥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያለመ ነው። አመልካቾች የተደራጀ የፕሮጀክት አመራርና የጥራት ማረጋገጥ ሂደት ሲያዩና በተሰጣቸው ምላሽ (በጉዳት ካሳ አሰራር) ሳይረኩ ሲቀሩ የጋራ ምላሽ አሰራር ይጠይቃሉ። ለተጨማሪ ማብራሪያ www.undp.org/secu-srm ይጎብኙ። ለዚህ የተዘጋጀ ቅፅ በዕቅዱ መጨረሻ ላይ ተያይዟል።

ቁልፍ አካባቢያዊና ማህበራዊ አመላካቾች

ይህ ክፍል ለፕሮጀክቱ ቁልፍ የሆኑ አካባቢያዊና ማህበራዊ አመላካቾችን የሚለይና የየራሳቸው የአስተዳደር አላማዎችን፣ ዐቅም ያላቸው ተፅዕኖዎችን፣ መቆጣጠሪያ ስራዎችን እና ከአመላካቾች አንፃር አካባቢያዊ የአፈፃፀም መስፈርቶችን (ለቁጥጥር የማያስቸግሩ) የሚያሳይ ነው። እንዲሁም ይህ ክፍል የቁጥጥር ሂደቱን ስኬትና ድክመት የማስተላለፍን አላማ ከአካባቢያዊ አፈፃፀም ጋር የመምራትና ሪፖርት የማድረግን አስፈላጊነት ያስገነዝባል፣ ቅኝት የሚፈልጉ ጉዳዮችን ለይቶ ያሳያል፣ በተጨማሪም በፕሮጀክት አመራር ላይ ተከታታይ ውጤት ሊያመጡ የሚችሉ እርምጃዎችን ያመላክታል።

ዕፅዋት እና እንስሳት

የተመረጡ ወረዳዎች ሰፊ የግብርና አካባቢ ጥናት ቀጠናዎችን ይሸፍናሉ። በዋና ዋና የግብርና ጥናት ቀጠናዎች መሰረት ወረዳዎች እንደሚከተለው ተከፍለዋል።

ሀ. ደረቅና ከፊል-ደረቅ ቀጠናዎች፡ ቢዮ አዋሌ፣ ገዋኔ፣ ጂግጂጋ፣ ቀብሪበያን፣ መዒሶ እና ዝዋይ ዱግዳ (ሞቃት ደረቅ ቆላዎች)፣ እና ገዋኔ (ሞቃት ደረቅ ቆላዎች)

ለ. ከፊል-ርጥብ አዳሚ ቱሉ-ጂዳ፣ ላስታ፣ ያሎ፣ ሳሲ ፅድ አምባ እና ታይታይ ኮራሮ (ሞቃትና ቀዝቃዛ ከፊል-ርጥብቆላዎች)

ሐ. ርጥብ፡ እነብሴ ምድር፣ ታች ጋይንት፣ ሶፊና ያቤሎ(ለስለስ ያለ ርጥበት መካከለኛ ቦታዎች)፣ እነብሴ ሳር ምድር (ቀዝቃዛ ርጥበት ከፍተኛ ቦታዎች) እና ጉባ (ሙቅ ርጥብ ቆላዎች) እና

መ. ሙቅና ሙቅ ከፊል-ርጥብ ዝቅተኛ ቦታዎች፡ አቦቦ፣ ኢታንግ፣ ማረቆ፣ ሃደሮ፣ ሃላባ

አብዛኞቹ የፕሮጀክቱ ቦታዎች ላይ እርሻ ዋናው የመሬት ጥቅም ነው። በነዚህ አካባቢዎች እርሻ (በተለያየ መጠን) ከ75-100 ፐርሰንት ይሸፍናል (ለፕሮጀክቱ በተሰራ የጥናት ዳሰሳ መሰረት)። በጂግጂጋና በዝዋይ-ዱግዳ ባሉ የፕሮጀክቱ ቦታዎች እርሻ የመሬቱን ከ60-70 ፐርሰንት ይሸፍናል፡ ቀሪው በተፈጥሮ አትክልቶች (ሳር ቅጠል) የተሸፈነ ነው። በጉባ፣ ሸርቆሌ፣ ገዋኔ፣ መኤሶ፣ ኢታንግ እና በአቦቦ መሬት የተሸፈነው በዋናነት በተፈጥሮ አትክልቶች (ሳር ቅጠል) ነው።

በተመረጡ ቀበሌዎች የመሬት ዋና ጥቅም እርሻ፣ ግጦሽና ደን/የማገዶ እንጨት ሲሆን በከፍተኛ መጠን የተራቆተ ነው። በየቀበሌዎቹ አብዛኞቹ ደኖች የግራር ዛፎች ይበዙባቸዋል። በፕሮጀክቱ ቦታዎች አካባቢ ዕፅዋትና እንስሳትን የተመለከተ ጥናት ባይሰራም በመሬት አጠቃቀምና በተፈጥሮ ሳር ቅጠል ላይ የተሰሩ

ጥናቶች እንደሚያሳዩት የክልሉ 70 ፐርሰንት በላይ መካን/ባዶ እንደሆነ ይገመታል(አፋር 2010)። ስለዚህ ውስን ቦታ በመኖሩ የሰዎች የጥቅም ፍላጎት ከፍተኛ የመሆን እድል አለው።

ኢትዮጵያ የተለያዩ ምርታማ ደኖችን ማልማት በተፈጥሮ ደኖችና የእንጨት ዛፎች ላይ ያለውን ጫና እንደሚቀንስ ተረድታለች። ይህም እየጨመረ ለሚሄደው የውስጥና የአካባቢ ፍጆታ ፍላጎት አስተማማኝና በአካባቢው በሚመረት እንጨትና ጣውላ በማይሆኑ ደኖች ያሟላል፣ አካባቢያዊ አገልግሎትና ምርት ይሰጣል። ዋና ዋና ተሳትፎዎች ከሌሎች ተግባሮች ጋር በማጣመር ችግኝ ማፍያ ጣቢያዎችን መመስረትንና ጣውላ የማይሆኑ ደኖችን ማስፋፋትን ያጠቃልላል። አብዛኞቹ የፕሮጀክቱ አካባቢዎች ምንም እንኳን በዕፅዋት ቢሸፈኑም ቀድሞ የባከኑ እንደሆኑ ይታሰባል። በተለይም የአየር ጣቢያዎች፣ ሰፋፊ እርሻዎችና የመስኖ ቦታዎች የተጠበቁና ጠቃሚ ቦታዎችን እንደማይዝ ይታሰባል። የተመረጡ ቦታዎችን ማልማት ከማንኛውም ስራ ቅድሚያ ይሰጠዋል።

የፕሮጀክቱ ስራዎች ደኖችን ማልማት፣ አካባቢዎችን በመከለል መልሶ ማልማትና የአፈር መሸርሸርና ጥበቃ እርምጃዎችን ያካትታል። እነዚህ ሁሉ ስራዎች ለአካባቢ በቀል እፅዋትና እንስሳት የተጓዳኝ ጥቅም ይሰጣሉ። የደን ጥበቃና አያያዝ ሂደቱ በትናንሽ የገጠርና የማህበረሰብ መሬቶች አነስተኛ ደረጃ የዛፍ ተከላ ላይ ያተኩራል።

የታቀዱ ስራዎች ትግበራ የተሳለጠ የመልከዓምድር አቀራረብ በመከተል ለሌሎች ጥበቃዎችና አገልግሎቶች መጠነ ሰፊ ጥቅም ይሰጣል።

የአፈፃፀም መስፈርት

ለፕሮጀክቶቹ ግንባታ የሚከተሉት የአፈፃፀም መስፈርቶች ተቀምጠዋል

ሀ. ከተከለሉ ቦታዎች ውጪ ዕፅዋት አይመነጠሩም
ለ. የለሙ አካባቢዎችንና የዘር አይነቶችን ማብዛት እና የስነ ምህዳር ፓራሜትርን ማገዝ (የአፈር መሸርሸርን መቀነስ፣ ንጥረ ምግብን መጨመር፣ የካርቦን ክምችትን መጨመር፣ የዉሃ ስርገትና ማቆር)
ሐ. በምንጠራ ምክኒያት አካባቢ በቀል እንስሳት አይሞቱም
መ. ምንም ዓይነት ጉዳት በውሃማና በየብስ አካባቢዎች አይከሰትም
ሠ. በግንባታ ስራና የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋሙ ዘሮችን በማልማት ወቅት አዳዲስ የአረም ዘሮች አይመጡም
ረ. በፕሮጀክት ስራ ምክንያት በፊት የነበሩ የአረም ዘሮች አይስፋፉም/አይሰራጩም።
ሰ. በአካባቢው ብቻ የሚገኙ ዝርያዎችን ያካተተ ውጤታማ የመልሶ ማልማት ስራ

ቁጥጥር

ለፕሮጀክቶቹ ቢያንስ በየሁለት ወሩ የሚገመገምና የሚታደስ የዕፅዋትና የእንስሳት ቁጥጥር ፕሮግራም ተዘጋጅቷል። በዋናነት በምንጠራ ጊዜ የሳይት ተቆጣጣሪው ለአካባቢና ደን ሚንስቴርና ለተመልፕ ሰራተኞች ሳምንታዊ ሪፖርት ያዘጋጃል።

ሀ. ለዕቅዱ የማያግዝ ማንኛውም ነገር
ለ. በቀደሙት ሳምንታት መልሰው የለሙ አካባቢዎች
ሐ. የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች ዝርዝር

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ
የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ሪፖርት ማድረግ

ሁሉም የዕፅዋትና የእንስሳት ቁጥጥር ውጤቶችና አጋጣሚዎች እቅዱ ላይ በተቀመጠው መልኩ በሰንጠረዥ ተሰርተው ሪፖርት ይደረጋሉ። በአካባቢው ብቻ የሚገኙ እንስሳት ሊሞቱ የሚችሉበት ሁኔታ ከታየና ዕፅዋት ከተጎዱ ለአካባቢና ደን ሚንስቴር ማሳዎቅ ግድ ይሆናል።

ሰንጠረዥ 1፡ የዕፅዋትና የእንስሳት አስተዳደር እርምጃዎች

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ሰንጠረዥ 1፡- የዕፅዋትና የእንስሳት አያያዝ እርምጃዎች

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
ዕዕ 1. የመኖሪያ ቦታዎች መጥፋትና የእንስሳት መረበሽ	ዕዕ 1.1. የተክሎች ምንጠራን መገደብና ያሉትን እፅዋት በበቂ ሁኔታ በመጠበቅና በማስተዳደር የመኖሪያ ቦታ ሁከትን መቀነስ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	ዕለታዊ ሪፖርትና መረጃ ማስቀመጥ
	ዕዕ 1.2. በግንባታ ወቅት የድምፅና የመብራት መጠንን ጥንቃቄ በሚፈልጉ ቅርብ ቦታዎች ላይ መቀነስ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	ዕለታዊ ሪፖርትና መረጃ ማስቀመጥ
	ዕዕ 1.3. ሁሉም የሳይት ሰራተኞች ስለ እንስሳት መኖሪያ ቦታዎች መረጃና ጥበቃ መረዳታቸውን ማረጋገጥ	በግንባታ ጊዜ	ስራ ተቋራጭ	ዕለታዊ ሪፖርትና መረጃ ማስቀመጥ
	ዕዕ 1.4. በአካባቢው ያሉ እንስሳትን ሁከት መቀነስና በግንባታ ወቅት ለተጎዱና ዎላጆቻቸውን ላጡ እንስሳት ማገገምና ማዳን መስራት	በግንባታ ጊዜ	ስራ ተቋራጭ	ዕለታዊ ሪፖርትና መረጃ ማስቀመጥ ለአካባቢና ደን ሚንስቴር ማሳዎቅ
ዕዕ 2. አዲስ የመጡ የእንስሳትና የዕፅዋት ዝርያዎች	ዕዕ 2.1. ከአረም፣ ተባይና በሽታ የፀዱ ተገቢ ዘሮችን በማቅረብና በማከማቸት የአዳዲስ አረም፣ ተባይና በሽታ መከሰትን መከላከል	በሁሉም ምዕራፎች	ሁሉም ሰራተኞች	መረጃ ማስቀመጥ
	ዕዕ 2.2. የአረምን በመሸርሸርና በደለል ምክንያት በውሃ መውረጃዎች ገብቶ መሰራጨትን ለመቀነስ የአፈር መሸርሸር፣ የተፋሰስና የደለል ቁጥጥር ዕቅድን መተግበር	በቅድመና በግንባታ ጊዜ	ስራ ተቋራጭ	መረጃ ማስቀመጥ

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ
የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
ዕዕ 2. አዲስ የመጡ የእንስሳትና የዕፅዋት ዝርያዎች	ዕዕ 2.3. የታወኩ አካባቢዎችን ከፍተኛ የመኖሪያ ቦታን በሚፈጥሩ በአካባቢው ብቸኛ በሆኑና በተለመዱ ዝርያዎች መልሶ ማልማት	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	እንዳስፈላጊነቱና መረጃ ማስቀመጥ
	ዕዕ 2.4. ጥላ የሚሰጡ ዛፎችን በማብዛት የአካባቢ ሁከትን መቀነስ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	ዕለታዊ ሪፖርትና መረጃ ማስቀመጥ
	ዕዕ 2.5. አካባቢ በቀል መልሰው የሚያድጉ ዛፍችን መቁረጥ መቀነስ፣ በተለይ ደኑ ስስ በሆነበት አካባቢ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	ዕለታዊ ሪፖርትና መረጃ ማስቀመጥ
	ዕዕ 2.6. ለትልልቅ ዛፎች እንዲጠቅም ትንንሽ ዛፎችንና ቁጥቋጦዎችን ማስወገድ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	ዕለታዊ ሪፖርትና መረጃ ማስቀመጥ
	ዕዕ 2.7. የሚወገዱ ተክሎች በሚገባ በቀለም ወይም በሚውለበለብ ማጣበቂያ ምልክት ይደረግባቸዋል	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	ዕለታዊ ሪፖርትና መረጃ ማስቀመጥ
	ዕዕ 2.8. አካባቢያዊ አረሞችና ጤናን የሚጎዱ አረሞች እግር በእግር ቁጥጥር ይደረግባቸዋል	በሁሉም ምዕራፎች	የሳይት ተቆጣጣሪ	ሳምንታዊ ሪፖርትና መረጃ ማስቀመጥ
	ዕዕ 2.9. ለተለዩ አካባቢዎች የደን አስተዳደር ዕቅድ ማዘጋጀትና መተግበር	በሁሉም ምዕራፎች	የአካባቢና ደን ሚንስቴር	መረጃ ማስቀመጥ
ዕዕ 3. ለበሽታና ለተባይ ተጋላጭነት	ዕዕ 3.1. የተዳቀሉ ዘሮችን በመጠቀም የበሽታና የጥቃት መከላከል አቅምን ማሳደግ	ትግበራ/ዘመቻ	የአካባቢና ደን ሚንስቴር	መረጃ ማስቀመጥ
	ዕዕ 3.2. የደን አስተዳደር ዕቅድ ለራስ እንዲመች ማድረግ - ማቅጠንና ማረምን ያካትታል	ትግበራ/ዘመቻ	የአካባቢና ደን ሚንስቴር	መረጃ ማስቀመጥ

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

የገፀ-ምድር እና የከርሰ-ምድር ውሃ ጥራት

ኢትዮጵያ በተለያዩ የመሬት አቀማመጦች ከሚለያይ ሰፊ የትሮፒካል ሞንሱን የአየር ንብረት ያላት ናት። አመታዊ የዝናብ መጠን በሶማሊያ እና በጅቡቲ ድንበሮች ከ100ሚሜ ያነሰ እና በደቡባዊ ምዕራብ ከፍተኛማ አካባቢዎች ከ2000ሚሜ የበለጠ ሆኖ በዚህ ውስጥ የሚገኝ ነው። (ስዕል 3) ብሔራዊ አማካይ የዝናብ መጠን 744ሚሜ በዓመት ነው።



ሥዕል 3. የኢትዮጵያ አመታዊ አማካይ የዝናብ መጠን[1]

ኢትዮጵያ ሦስት ዓየርንብረታዊ የዝናብ ወቅቶች ያሏት ሲሆን በስም ከየካቲት እስከ ግንቦት (በልግ)፣ ከሰኔ አስከ መስከረም (ክረምት)፣ ከጥቅምት እስከ ጥር (በጋ) ወቅቶች ናቸው። የወቅታዊ የዝናብ መጠን ልዩነት ላይ ከሰሜን ወደ ደቡብ በሚኖረው ኢንተር-ትሮፒካል ኮነቨርጀንስ ዞን በአብዛኛው ተጽዕኖ አለው። በደቡብምዕራብ ኢትዮጵያ ከመጋቢት እስከ ጥቅምት የሚቆየው እርጥበታማው ወቅት ለእነዚህ ሁኔታዎች ሰፊ ምሳሌ ይሆናሉ። ስምጥ ሸለቆ እና አጎራባች ክፍሎች በጠቅላላው ሁለት ዝናባማ ወቅቶችን፡- አነስተኛ (ከመጋቢት እሰከ ግንቦት) እና ዋና (ከሰኔ እስከ መስከረም) በደረቃማ ወቅቶች የሚቋረጡ ናቸው። ጊዜያዊ የዝናብ መጠን ልዩነቶች ስከሰቱ የኢትዮጵያ ክፍሎች በከፍተኛ ሁኔታ ለድርቅ ይጋለጣሉ ማለት ነው።

ተያያዥ ተጽዕኖው ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ በደጋማ ቦታዎች ይጥልና በወንዝ ሸለቆዎች ገብቶ ዓመታዊ የዝናብ መጠናቸው ዝቅተኛ ወደ ሆነው ቆላማ አካባቢዎች ይፈሳል፡፤ በኢትዮጵያ ባሉት ሁሉም ወንዝ ሸለቆዎች በሚያስብል መልኩ 80 በመቶ የሚሆነው የውሃ ፍሳሻቸው ከሰኔ እስከ ጥቅምት ባሉት አራት ወራት ከሚጥለው ዝናብ ነው። በኘሮረቶች የውሃ ፍሰት መጠንን ሁለት የምክንጣት ስብስቦች የሚወስኑት ሲሆን እነዚህም ዓየርንብረታዊ እና የማፋሰሻ ሸለቆዎች አከላለዊ ባህሪያት ናቸው።

[1] http//rehefweb.int/map/Ethiopia-annual-rainfall

የከርሰምድር ውሃ በኢትዮጵያ ጠቃሚ የውሃ መገኛ ሲሆን በብዙ አካባቢዎች በተለይም የገጽታ ውሃ እጥረት ያላበት እና ወቅታዊ በሆኑባቸው ደረቃማ አካባቢዎች ዋነኛው ለቤት ፍጆታ አቅርቦት የሚሆን ነው። ሥዕል 4 በመላው ሀገሪቱ ያለውን ሰፊ የከርሰምድር ውሃ ያሳያል።



ሥዕል 4፡- የከርሰምድር ውሃ የሚገኝበት ግምት፡ እነ ማክዶናልድ፣ 2001[2]

ለከርሰምድር ውሃ መልሶ መሙላት የዝናብ የትልቀት መጠን ጉልህ ሚና ይጫወታል። ለሰፊው የከርሰምድር ውሃ ሥርዓት ዋነኛው የመልሶ መሙያ ምንጭ በደጋማው ክፍል ያለው ዝናብ ነው። ዋንኛው የመልሶ መሙያ ዞን በክልል ደረጃ ከኢትዮጵያ ደቡብ ምስራቅ ደጋማ ክፍል ነው።

ጂኦሎጂ ለከርሰምድር ውሃ ስርጭት እና መከሰት ጠቃሚ ሚና እንደሚጫወት እና ገፀ-ምድር የውሃ ጥራት ላይ ውጤት ሊኖረው እንደሚችል በደንብ የሚረዱት ጉዳይ ነው። በውሃ ናሙናዎች ውስጥ የተጓጓዙት የሚሙ ንጥረ ነገሮች ክምችቶች፣ አንጻራዊ ምጥጥኖሽ እና ምጣኔዎች የመነሻቸውን መንገድ እና የተለያዩ ንጥረ ነገሮችን ያንጸባርቃሉ። የፕሮጀክት አካባቢው ጂኦሎጂ ካርታ እና የከርሰምድር እምቀት ዳሰሳ ተስርቷል።

በዋና ዋና ካሽኖች እና አየኖች ላይ በመመስረት የውሃ ኃይድሮ-ኬሚካል ምደባ በፕሮጀክት አካባቢው ያለው የከርሰምድር ውሃ የቤዚክ፣ ትራንዚሽናል እና ድብልቅ ዓይነት የውሃ ውህዶች እንደሆነ ያመላክታል። በአብዛኞቹ የኢትዮጵያ ውሃዎች ባይካርቦኔት (HCO3) ዓይነት ዋነኛው ካሽን ሲሆን ባጠቃላይ እንደ ኖራ፣ ዶሎማይት፣ አሸዋ፣ ሲልከን እና ሌሎች ማዕድናት ያሉት ዐለቶች መኖር የባይካርቦኔት (HCO3) ቸየኖች ምንጮች ናቸው።

[2] NacDonald, A.M., Calow, R.C., Nicol, A., Hope B, and Robins, N.S. 2001 Ethiopia: □□□ □□□□ □□ □□□□□ □□□□ □□□□□ □□□□ WC/01/02

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

በኢትዮጵያ የከርሰምድር ውሃ ጥራት ከፍተኛ ልዩነት እንዳለው የሚታወቅ ነው ይኸውም ከክርስታል ቤዝመንት ዐለቶች ከሚነሱት ከብዙ ጅረቶች ንጹህ ውሃ እሰከ ስምጥ ሸለቆ እና ሴዲመንተሪ ሜዳዎች የየሚነሱት ጨዋማ የሆነ ውሃ።

በስምጥ ሸለቆ ዞን ያለው የከርሰምድር ውሃ ባልተለመደ ከፍተኛ የፍሎራይድ እና/ወይም ሙሉለሙሉ የሟሟ ጨው ከፍተኛ ክምችት ያለው የጂኦተርማል ውሃ ተጽእኖ ያለበት ነው። ስለዚህ ፍሎራይድ በተለይም በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ለሚኖሩ ማህበረሰቦች የታወቀ ከፍተኛ ችግር ነው። በብዙዎቹ የከርሰምድር ውሃዎች በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ከሴድመንቶች የጨመረ ጨው መታየት በሴድመንቱ አንዳንድ ሆሪዞኖች የሚመነጨው የሚተኑ ማዕድናት (የመትነን ውጤቶች) መሟሟት ነው። ልክ እንደ አብዛኞቹ የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ ሌሎች ክፍሎች ፍሎራይድ በኢትዮጵያም የታወቀ ከውሃ ጋር የተያያዘ ችግር ነው።

ዘርፈ ብዙ የሰው ልጅ እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ የደን ምንጣሮ፣ ከልክ በላይ የተፈጥሮ ሀብትን መጠቀም፣ ብክለት እና ባዕድ የሆኑ ዝርያዎች ያለልክ መሰራጨት መሬቶችን እንዲቦረቦሩ እና ምርታማነት እንዲቀንስ አድርጓል። ከከፍተኛ የዝናብ መጠን ልዩነት እና የእጽዋት ሽፋን መቀነስ ጋር ተዳምሮ የውሃ ጥራት ጥያቄዎችን አስነስቷል።

በታለሙት ወረዳዎች ውስጥ አነስተኛ መጠን ያላቸውን የመስኖ ሥራዎች፣ ባህላዊ የመስኖ አሰራሮችን ማሻሻልን የማስቀየሻ ሽቦዎችን መገንባትን እና በቧንቧ የተደገፉ የመስኖ ሥራዎችን ማጎልበትን አካቶ የተጣመሩ ሥራዎች ታቅደዋል። ፕሮጀክቱ ከዚህም በተጨማሪ ከላይ የተጠቀሱትን ሥራዎች የሚያጣምር ሲሆን ይህም በታለሙት ማህበረሰቦች የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮን፣ ጠባብ የውሃ ጉድጓዶችን መገንባትን እና በሶላር ኃይል የሚንቀሳቀሱ ጠላቂ እና የገጽታ ውሃ ፓምፖች መትከልን ያካተተ በፀሃይ ኃይል የሚንቀሳቀሱ ፓምፕ የማድረጊያ ሲስተሞችን በመጠቀም የከርሰምድር ውሃን ተደራሽ ማድረግ ነው።

የውሃ ብክለት ምንጮች የሚከተሉትን ያካትታሉ

ሀ. የአፈር መሸርሸር፤
ለ. በውሃ ውስጥ የፌካል ኮሊፎርም መኖር ዋንኛው ምክንያት ዝቅተኛ የውሃ ንጽህና ልማዶች ናቸው፤
ሐ. ቆሻሻ ጎርፍን፣ የኤችፒ ለውጥን፣ ከባድ ብረቶችን እና ሌሎች ዓይነት በካዮችን፤ የግብርና ኬሚካሎችን፣ የማደበሪያ ፍሰትን፣ ዘይትን፣ ደረቅ ቆሻሻን ወዘተ አካቶ ብዙ የሰው ልጆች እንቅስቃሴዎች ብክለትን ይጨምራሉ፤
መ. የቆሻሻ ማሰወገጃ፣ ከማሽነሪዎች የሚፈስ ዘይት እና ደረቅ ቆሻሻ ማሰወገጃ ግንባታን አካቶ
ሥራዎቹ ከመጀመራቸው በፊት ተስማሚ የመቆጣጠሪያ ዘዴ ለማጎልበት የመነሻ ውሂብ/ዳታ የሚሰበሰብ ይሆናል።

የአፈጻጸም መስፈርቶች

የሚከተሉት የአፈጻጸም መስፈርቶች ፤ፕሮጀክቱ ግንባታ የተቀመጡ ናቸው፡-

ሀ. በግንባታ እና ኦፕሬሽን ሥራዎች የተነሳ ምንም ዓይነት ጉልህ የውሃ ጥራት መቀነስ መኖር የለበትም
ለ. በፕሮጀክቱ አቅራቢያ በግንባታ እና ኦፕሬሽን ሥራዎች የተነሳ በገጸ ምድር እና/ወይም ከርሰምድር ውሃ ምንም ዓይነት ጉልህ የውሃ ጥራት መቀነስ መኖር የለበትም።
ሐ. የውሃ ጥራት በዩኤንዲፒ፣ በሜፈክ፣ እና/ወይም በሌላ የመንግስት አካላት ከተደነገጉት ማናቸውንም የጸደቁ ሁኔታዎች ጋር መጣጣም አለባቸው፤ ወይም እንዲህ ዓይነቶቹ ሁኔታዎች በማይኖሩበት ጊዜ አለማባስ ዘዴን¡ ይከተሉ፤ እና

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

መ. ለሳይቱ ተስማሚ የሆነ ኢ.ዲ.ኤስ.ሲ.ፒ በውጤታማነት መፈጸም።

በዚህ ዕቅድ የተቀመጡትን የአያያዝ እርምጃዎች በመከተል ፕሮጀክቱ በሰፊው አካባቢ በውሃ ጥራት ላይ ጉልህ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ አይኖረውም።

ቁጥጥር

ለፕሮጀክቱ ደረጃውን የጠበቀ የውሃ ጥራት መቆጣጠሪያ ፕሮግራም ጎልብቷል። ፕሮግራሙ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ በየሦስት ወሩ የሚከለስ እና ሚሻሻል ይሆናል። የሳይቱ ተቆጣጣሪ በየዕለት የሳይት ቁጥጥር ማረጋገጫ አካልነት በሥራው አቅራቢያ ወይም አካባቢ ለናይትሬት፣ ለፎስፌት፣ ለፌካል ኮሊፎርም፣ ለድብክብክነት(ቆሻሻ ጎርፍ)፣ ለከባድ ብረቶችን እና ዘይት/ግሪስ አግባብነት እይታዊ ምርመራ ማድረግ እና የውሃ ናሙና መውሰድ ይጠበቅበታል።

ሪፖርት ማድረግ

የውሃ ጥራት ቁጥጥር ውጤቶች በሰንጠረዥ ተሰርተው እቅዱ ላይ እንደተገለፀው ሪፖርት መደረግ አለባቸው። መሳሪያዎች ወይም አካባቢ ላይ ከባድ ጉዳት ሊያመጣ ይችላል ተብሎ የሚጠረጠር አጋጣሚ ሲታይ ወይም ከተወሰነው የውሃ ጥራት ካለፈ ወዲያውኑ ለአካባቢና ደን ሚንስቴር መገለፅ አለበት።

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ሰንጠረዥ 2፡- የውሃ ጥራት አስተዳደር እርምጃዎች

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
ው 1. ከፍ ያሉ/የተቋጡ ጠጣር ነገሮች፣ ጨዋማ ናይትሬቶች፣ ማዳበሪያ/ፎስፌት፣ የአንጀት ባክቴሪያዎች፣ከባድ ብረቶች፣ ደለልና ወለል ላይ የሚወጣ ቆሻሻ ጎርፍ እና የመሬት ውስጥ ውሃ	ው 1.1 የተፋሰስ፣ የደለል/ዝቃጭ እና የአፈር መሸርሸርን ለመቆጣጠር ልዩ የሳየት ዕቅድ ማዘጋጀትና መተግበር። ለሁሉም የፕሮጀክቱ ስራዎች የሚሆኑ እቃዎችን (አፈርን ጨምሮ) ለመጠባበቂያ ማከማቸት። ሁሉም መሳሪያዎች በትክክል መስራታቸውን ለማረጋገጥ እርምጃዎች በመደበኛ ሁኔታ ይፈተሻሉ።	ቅድመ የመሬት ስራዎች	የሳይት ተቆጣጣሪ	መጀመሪያ በተዘረጋው አሰራር እና እንዳስፈላጊነቱ ለተ.መ.ል.ፕ እና ለአካባቢና ደን ሚንስቴር ማሳወቅ
	ው 1.2 ነዳጅ፣ ዘይት፣ ኬሚካልና ሌሎች አደገኛ ፈሳሾች በደንብ በተለየ፣ በጥቅል የታጠረ፣ ሌሎች ስራዎች የማይሰሩበትና ከፍሳሽ የፀዳ ቦታ ሊዘጋጅላቸው ይገባል። ነዳጅ የሚሞላው ከውሃ ቦታዎች ርቆ ነው።	በግንባታ እና በዘመቻ ምዕራፍ	ሁሉም ሰራተኞች	ሳምንታዊና ለተ.መ.ል.ፕ እና ለአካባቢና ደን ሚንስቴር ማሳወቅ
	ው 1.3 የከርሰምድር ውሃ ላይ ተፅዕኖ ሊደርስ የሚችልበት ቦታ ላይ መደበኛ የወለልና የከርሰምድር ውሃ ጥራት ቁጥጥር ማድረግና የከርሰምድር ውሃው ጥራት ላይ የመጣውን ለውጥ መከታተል።	በግንባታ እና በዘመቻ ምዕራፍ	የሳይት ተቆጣጣሪ	ሳምንታዊና ለተ.መ.ል.ፕ እና ለአካባቢና ደን ሚንስቴር ማሳወቅ
	ው 1.4 የታወኩ አካባቢዎችን መልሶ ከማልማትና ከማረጋጋት ጀምሮ ስራዎችን በጊዜ ሰሌዳ ማቀድ	ቅድመ የመሬት ስራዎች	የሳይት ተቆጣጣሪ እና የአካባቢና የደን ሚንስቴር	መረጃ ማስቀመጥ
	ው 1.5 አካባቢ ላይ የሚያስከትሉትን ጉዳት ለመቀነስ የግንባታ እቃዎች ውሃማ አካባቢዎች አጠገብ አይከማቹም። ከባድ ዝናብ ከተተነበየ ከእያንዳንዱ የስራ ቀን በኋላ ከውሃማ አካባቢ ይርቃሉ/ይነሳሉ።	በግንባታ እና በዘመቻ ምዕራፍ	የሳይት ተቆጣጣሪ	ዕለታዊ መረጃ ማስቀመጥ

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

የመሬት መሸርሸር፣ ተፋሰስ እና ዝቅጠት ቁጥጥር

የፕሮጀክቱ አካባቢ አፈሮች ጂአይኤስን በመጠቀም በካርታ ተቀምጠዋል። አስራ ሰባት ዋና ዋና የአፈር ዓይነቶች ተስተውለዋል።

ሌፕቶሶልስ በ16 በፕሮጀክቱ አካባቢ በዋናነትም በታችጋይንት (92%)፣ ላስታ (93%)፣ እና ቢሎ-አዌ (77%) በመገኘት በስፋት የተሰራጩ ናቸው። ሌፕቶሶልስ በተጨማሪም የታይታ ቀራሮን፣ የሳሲ-ጸዳምባን እና እነበሴ-ሳርምድርን ከ30-40% ይሸፍናሉ። ካምቢሶልስ አብዛኞቹን የፕሮጀክት አካባቢዎች በበላይነት (24%) ይይዛሉ እና በከፍተኛ መጠን በጅግጅጋ (54%)፣ በቀብራ-በያህ (56%) እና በሃላባ (45%) ይገኛሉ። የፕሮጀክት አካባቢውን 13 % የሚሸፍኑት ቭርቲሶልስ በጅግጅጋ፣ አቦቦ እና ኢታንግ አካባቢዎች ከ23-37% የሚሆነውን ይይዛሉ። የፕሮጀክት አካባቢውን 10 % የሚሸፍኑት ኒቲሶከልስ በከፍተኛ መጠን (82%) በሸርኮሌ ይገኛሉ። ሉቪሶልስ በዋናነት በማረቆ እና ሶፊ የሚገኙ ሲሆን በአነስተኛ መጠን በየሳሲ-ጸዳምባ፣ ሚኤሶ፣ ጉባ፣ እነበሴ-ሳርምድር እና ሃላባ አካባቢዎች ይገኛሉ።ፍሉቪሶስ በፕሮጀክት አካባቢው ምዕራባማ ክፍሎች ማለትም ኢታንግ፣ አቦቦ፣ ጉባ፣ ሸርኮሌ እንዲሁም ገዋኔ እናያቤሎ አካባቢዎች ይገኛሉ።

ሌሎቹ ዋና ዋና የአፈር ዓይነቶች ከፕሮጀክቱ አካባቢ ከሁለት በመቶ በታች የሚይዙ ሲሆን በአንድ ወይም ሁለት ሳይቶች የተወሰኑ ናቸው፤ አንዶሶሎች በአዳሚ ቱሉ- ጂዶ- ኮምቦልቻ እና ዝዋይ ዱግዳ፤ ሬጎሶልስ በገዋኒ እና መኢሶ፤ አክሪሶልስ በጉባ እና ሸኮሌ፣ ፕሊንቶሶልስ እና ፕላንቶሶልስ በአቦቦ እና ኢታንግ፤ እና ካሊክሶልስ በቀብሪበያህ፣በአጠቃላይ ግሌይሶልስ፣ ሶሎሜዝ፣ አሬኖሶል እና አሊሶል በፕሮጀክት አካባቢዎቹ ውስጥ በጣም በአነስተኛ መጠን የሚገኙ ናቸው። እነዚህ ዋና ዋና የአፈር ዓይነቶች በአካባቢዎቹ ውስጥ፣ ለምሳሌ በአዳሚ ቱሉ-ጂዶ- ኮምቦልቻ፤ ታህታይ-ቀራሮ፣ ሳሲ-ጸዳንባ፣ ኢታንግ እና ሶፊ 2-7% ሽፋን ሲኖራቸው የአነዚህ ልዩ ሁኔታ 32% ሽፋን ያለው በአላባ የሚገኘው አርኔሶል ነው።

የአፈር መሸርሸር በብዙ መለኪያዎች፣ ለምሳሌ የአፈሩ ዓይነት፣ የመሬት ተዳፋት፣ የዕጽዋት ሽፋን፣ የመሬቱ አቀማመጥ ባሕርይ፣ እና የዝናብ መጠን ላይ የሚመሠረት ይሆናል። የአፈር ጥንካሬ ማጣት እና የአፈር መሸርሸር የዕጽዋት ሽፍን በመመንጠሩ እና በብዙ የግንባታ ሥራዎች ሊከሰቱ ይችላሉ። ይህም የአፈርን ለምነት ማሳጣትን እና የመሬት ተዳፋትነት እንዳይጠበቅ ማድረግን ሊያስከትል ይችላል። ለፕሮጀክቱ መሬት ማዘጋጀት በአካበቢው ላይ የውሃ ማፋሰሻ ሁኔታዎች ለውጦችን በማስከተል የተፈጥሯዊ የውሃ ፍሰት አቅጣጫዎችን ሊዘጋ ወይም ሊያስቀይር ይችላል። ውጤታማ እና ብቁ የመቀነሻ እርምጃዎች እነዚህን ሁኔታዎች መቀነስ ብቻ ሳይሆን አሁን ያሉትንም ሁኔታዎች ሊያሻሽሉ ይችላሉ።

ፕሮጀክቱ አካላዊ እና ስነ ሕይወታዊ የውሃ እና አፈር ጥበቃ ሕክምናዎችን፣ የደን መመናመን ያለባቸውን መሬቶች ወደ በደን መሸፈንን የደን ተከላን ማስፋፋትን የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓዶች ማጎልበትን፣ አነስተኛ መጠን ያላቸው የመስኖ ስራዎችን ማጎልበትን፣ የአየር መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችን እና ሕንጻዎች ግንባታን ያከናውናል። እነዚህ ሁሉም እንቅስቃሴዎች በአግባቡ ካልተያዙ ለአፈር መሸርሸር ዋነኛ መንስዔዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ለአፈር መሸርሸር ትልቅ መንስዔ የሚሆኑ ሥራዎች የአየር ንበረቱን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚሰሩ ይሆናሉ። ምስል 5፣ ለእያንዳንዳቸው የፕሮጀክት አካባቢዎች ዓይነተኛ ወርሃዊ የዝናብ መጠንን ያሳያል።

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ
የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል



እ. ሳር ምድር



ሳሲ-ጸዳምባ



ላስታ



ጉባ



ታህታይ-ቀራሮ



ያሎ



ሸርኮሌ



ታች ጋይንት



ገዋኔ



ማረቆ



መኤሶ



ጂዶ ኮምቦልቻ



ድሬዳዋ



ኢታንግ



ዝዋይ ዱግዳ



ሐረር



አቦቦ



አሳባ



ጅግጅጋ

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ
የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል



አላባ



ሃዳሮ ቱንቲ



ቀብሪ በያህ

የአፈጻጸም መስፈርቶች

የሚከተሉት የአፈጻጸም መስፈርቶች ለፕሮጀክቶቹ ግንባታ የተቀመጡ ናቸው፡-

ሀ. በውሃማ አካባቢዎች እና/ወይም በገጽታ እና/ወይም በከርሰ ምድር ውሃ በግንባታ ወይም በኦፕሬሽን ስራዎች የተነሳ የዝቃጭ ክምችት አይኖርም።

ለ. በሁሉም ፕሮጀክቶች ሳይት ላይ ወይም ከሳይት ውጪ የውሃ ጥራት መቀነስ አይኖርም።

ሐ. በፕሮጀክት ሳይቱ እና/ወይም በከርሰ ምድር ውሃ ሥርዓቶች የሚነረው ሁሉም ውሃ በተሻለ የአፈር መሸርሸር፣ የውሃ ማፋሰሻ እና የዝቃጭ መቆጣጠሪያ አሠራር ማለፍ አለባቸው፤ እና

መ. ለሳይቱ ተስማሚ የሆነ የአካባቢና የማህበራዊ አያያዝ ዕቅድ በውጤታማነት መፈጸም።

በዕቅዱ የተቀመጡትን የአያያዝ እርምጃዎች በመከተል ፕሮጀክቱ በሰፊው አካባቢ በውሃ ጥራት ላይ ጉልህ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ አይኖረውም።

ቁጥጥር

ለፕሮጀክቱ ደረጃውን የጠበቀ የውሃ ጥራት መቆጣጠሪያ ፕሮግራም ጎልብቷል። ፕሮግራሙ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ በየሦስት ወሩ የሚከለስ እና የሚሻሻል ይሆናል። የሳይቱ ተቆጣጣሪ የሚከተሉትን መፈጸም ይጠበቅበታል፡-

ሀ. በየሳምንቱ ወይም በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ 20 ሚሜ የሚበልጥ ዝናብ ከዘነበ በኋላ የሳይት ፍተሻዎችን ያካሂዳል።

ለ. ከዚህ ዕቅድ ወይም ከማንኛውም አግባብነት ካለው የኢ.ዲ.ኤስ.ሲ.ፒ ጋር ለማይጣጣሙ ከሳይቱ ጋር ተስማሚ የሆነ የማረጋገጫ ሰነድ ያጎለብታል።

ሐ. የምርመራዎቹን ውጤቶች እና/ወይም በሳይት ተቆጣጣሪው በውሃ ጥራት ላይ የተደረጉ ፍተሻዎችን ውጤቶች ይገልጻል እና ከቁጥጥር ማነስ ጋር የተያያዙ ማናቸውም ችግሮች ወዲያኑ መስተካከላቸውን ያረጋግጣል እና ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይደገሙ ሂደቶች መቀመጣቸውን ያረጋግጣል።

የሳይት ተቆጣጣሪው የሚከተሉትን የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡-

ሀ. በየዕለት የማጣራት አሠራር አካልነት የኢ.ዲ.ኤስ.ሲ.ፒን የቁጥር እርምጃዎች ለማረጋገጥ የዕለት ፍተሻዎችን ያካሂዳል፤ እና

ለ. አለመጣጣም በሚጠረጠርበት ጊዜ የአካባቢና የደን ሚንስቴርንና የተመልጥ ሠራተኞችን ያማክራል እና በዚሁ መሠረት ያሻሽላል።

ሪፖርት ማድረግ

ሁሉም የዝቅጠት እና የአፈር መሸርሸር መከታተያ/መቆጣጠሪያው ውጤቶች/ከስተቶች በሰንጠረዥ የሚቀመጡ እና በዕቅዱ እንደተቀመጠው ሪፖርት የሚደረጉ ይሆናሉ። የአካባቢ ሚንስቴሩ ማናቸውም የሚጠረጠሩ የማቴሪያል ክስተቶች ወይም ከፍተኛ አካባቢን የሚጎዱ ነገሮች በሚከሰቱበት ጊዜ ወይም የአፈር መሸርሸርን እና የዝቅጠት መቆጣጠሪያን በተመለከተ ከተወሰነው ደረጃ ከበለጠ ወዲያውኑ ሊገለጽለት ይገባል።

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ሰንጠረዥ 3፡- የአፈር መሸርሸር፣ ዝቅጠት መቆጣጠሪያ እርምጃዎች

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
አ1፡ ከገጽታ እና/ ወይም ከከርሰ ምድር የውሀ ስርአቶች በመሬት ጠረጋ ስራዎች የተነሳ መዛባት እና የአፈር ቁሳቁሶች መታጣት፣ ዝቅጠት	አ. 1.1 ለማናቸውም የገፀምድር ስራዎች፣ ግድቦች እና የቁፋሮ ስራዎች፣ የውሀ ማለፊያዎች እና የዝናብ ውሀ ማለፊያዎች በእቅዱ ማጎልበት እና መፈጸም	በግንባታ ምዕራፍ	ሁሉም ሰራተኞች	የመያዣ መዛግብት
	አ. 1.2 የአፈር መሸርሸር እና የዝቅጠት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች መተከላቸውን፣ እንደ አስፈላጊነቱ መፈተሸቸውን እና መጠገናቸውን መቆጣተር	በግንባታ ምዕራፍ	የሳይት ተቆጣጣሪ	የመያዣ መዛግብት
	አ 1.3 የሚመነጠሩ አካባቢዎችን እና ተጋላጭ የሆኑ አፈሮችን በሁሉም ጊዜያት ለመቀነስ የደራጃ ስራዎች	በቅድመና በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	የመያዣ መዛግብት
	አ 1.4 ለሁሉም ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች እና የማፋሰሻ መስመሮች ጊዜያዊ እና ቋሚ የኢ.ዲ.ኤስ.ሲ እርምጃዎችን ንድፍ እና የሚሆኑበትን ቦታ ማካተት። እነዚህ መፈጸም ያለባቸው ከቅድመ የግንባታ ስራዎች በፊት ሆኖ በስራ ጊዜ በሳይቱ መኖር አለባቸው።	በቅድመና በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	የመያዣ መዛግብት
	አ 1.5 በዝቅተኛ ዘናብ እና ከፍተኛ ንፋስ ወቅቶች ዋና ዋና የእጽዋት ምንጣሮ እና የመሬት ምንጣሮ ስራዎች እንዳይሰሩ ማረጋገጥ	በቅድመና በግንባታ ጊዜ	ተቋራጭ	የመያዣ መዛግብት
	አ 1.6 መሬቱን እንደገና በደን በማልበስ ጊዜ እና/ወይም የተወገደ አፈርን ወደ ግብርና መሬት ለመመለስ የላይኛውን አፈር መጥረግ እና ከምሮ መያዝ	በቅድመና በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	የመያዣ መዛግብት
	አ 1.7 የላይኛውን አፈር መቆለል ለመቀነስ የሚያስፈልጉ ስራዎችን መስራት። ለረጅም ጊዜ ክምችት ካስፈለገ የእጽዋት ክምችት መያዝ	በቅድመና በግንባታ ጊዜ	ሁሉም ሰራተኞች	የመያዣ መዛግብት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ
የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
አ1፡ ከገጽታ እና/ ወይም ከከርሰ ምድር የውሀ ስርአቶች በመሬት ጠረጋ ስራዎች የተነሳ መዛባት እና የአፈር ቁሳቁሶች መታጣት፣ ዝቅጠት	አ 1.8 የመከመሪያ አካባቢዎችን ከማፋሰሻ መሄጃዎች ከውሀ መሄጃዎች እና ከሚጎዱ ቦታዎች ማራቅ	በቅድመ ግንባታ እና በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	የመያዣ መዛግብት
	አ 1.9 የውሀ ፍሰት ቬሎሲቲ ለመቀነስ እና እምቅ/ ከባድ የውሃ ፍሰትን ለማስወገድ የዝናብ ውሃ አያያዝን መንደፍ	በቅድመ ግንባታ እና በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	የመያዣ መዛግብት
	አ 1.10 የውሀ ፍሰት ቬሎሲቲዎችን ለመቀነስ እና ዝቅጠትን በተወሰነ ለማጣራት አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ በማፋሰሻ መስመሮች የመቆጣጠሪያ ግድብን ማካተት። የመቆጣጠሪያ ግድቦቹን በመደበኛነት መፈተሽ እና መጠገን።	በቅድመ ግንባታ እና በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	የመያዣ መዛግብት
	አ 1.11. ሙሉቺንግ የአፈር መሸርሸር እና ዝቅጠት መቆጣጠሪያ ሆኖ ጥቅም ላይ ሊውል ሲችል በማናቸውም የመሬት ተዳፋቶች ከዋለ (በሳይት መረጣው ላይ በመመስረት) ከፍተኛ ዝናብ በሚኖርበት ጊዜ ተጨማሪ የዝቃጭ መከላከያ ይካተት።	በግንባታ ጊዜ	ሁሉም ሠራተኞች	የመያዣ መዛግብት
	አ 1.12 በንዲንግ በውሃ መሄጃዎች ውስጥ ወይም በሚጎዱ/አደገኛ እቃዎች አካባቢ ጥቅም ላይ መዋል አለበት	በሙሉ ግንባታ	ሁሉም ሠራተኞች	የመያዣ መዛግብት
	አ 1.13 የሳር ማጣሪያ የውሃ ቬሎሲቲን ለመቀነስ በግንባታ ጊዜ አስፈላጊ ከሆነ መካተት አለበት	በሙሉ ግንባታ	የሳይት ተቆጣጣሪ	የመያዣ መዛግብት
	አ 1.14 የዝቃጭ መከላከያ ወይም ተመሳሳይ መዋቅሮች የጨመረ የዝቃጭ መጠን በሚኖርበት ጊዜ ለመከላከል መገጠም አለበት	በግንባታ ጊዜ	ተቋራጮች	የመያዣ መዛግብት
	አ 1.15 በቂ የማያዝ አቅም ለመፍጠር አስፈላጊ ሲሆን በሁሉም የአፈር መሸርሸር እና ዝቃጭ መቆጣጠሪያ መዋቅሮች ጠጨማሪ አለት መኖር አለበት (ለምሳሌ የሴድመንት ቤዚኖች፣ መቆጣጠሪያ ግድቦች)	በግንባታ ጊዜ	ተቋራጮች	የመያዣ መዛግብት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
አ1፡ የአፈር መበከል	አ 2.1. ብክለት ካልታየ ወይም ከተጠረጠረ (ከፕሮጀክቱ ውጪ) ደረጃ 1 የመጀመሪያ የሳይት ብክልት ምርመራ ይደረግ። ተቋራጩ ቀድሞ ያልተገኘ ብክለት ከገጠመው ሥራ ማቆም አለበት እና የአስተዳደር አሰራሮችን በመጀመር ምክር/ፈቀድ/ማጽደቅ (እንደአስፈላጊነቱ) ማግኘት አለበት	በግንባታ ምዕራፍ	ሁሉም ሰራተኞች	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	አ 2.2 በፕሮጀክቱ ክልል ውስጥ ያለ የተበከለ አፈርን አካቶ ከሳይቱ የተበከለ አፈርን/ቁሳቁስን ለማንሳት እና ለማስወገድ (የሚያስፈልግ ከሆነ) የተመረጡ አሰራሮችን መከተል	በግንባታ ምዕራፍ	ሁሉም ሰራተኞች	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	አ 2.3 የሚፈስ ውሃ ከተበከሉ አካባቢዎች ጋር (በፕሮጀክቱ ክልል ውስጥ ያለ የተበከለ ቁሳቁስን አካቶ) አለመገናኘቱን ለማረጋገጥ የተፋሰስ ቁጥጥር እርምጃዎችን መውሰድ	በግንባታ ምዕራፍ	ሁሉም ሀሰራተኞች	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	አ 2.4 ከሌላ ቦታ መጥተው የሚጠቀጠቁ/የሚሞሉ ሳይቱን የሚበክሉ ከሆነ እና ከብክለት ነጻ ለመሆናቸው ማረጋገጫ/ሰነድ የሌላቸው ከሆነ እነዚህኑ መጠቀምን ማስወገድ።	በግንባታ ምዕራፍ	ሁሉም ሰራተኞች	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ
የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ድምጽ እና መርገብገብ

ሁሉም የግንባታ እና የኦፕሬሽን ስራዎች የድምጽ ብክለት/ሁከት የመፍጠር የታመቀ አቅም አላቸው። በአካቢው ላሉ ነዋሪዎች እና ስሱ እንስሳት የእርግብግቢት ረብሻ ከእርግብግቢት የሚፈጥሩ መሣሪያዎች ከመጠቀም የመከሰት እድል አላቸው። በዚህ ፕሮጀክት አካልነት ፍንዳታ እንዲደረግ አይፈለግም።

የፕሮጀክት ሥራዎቹ የሚፈጸሙት በዋናነት የገጠር ባሕርይ ባላቸው አካካቢዎች (ለግብርና ስራ እና ለግጦሽ የሚውሉ) ወይም የደን መሬት በመሆናቸው አሁን ያለ ጉልህ የድምጽ ረብሻ የላቸውም። ማሽነሪዎችን መጠቀም ወይም ድምጽ የሚያወጡ መጠቀሚያዎችን ወደ ቦታው ማምጣት በአካባቢው ላይና በአካባቢው ነዋሪዎች በትክክሉ ካልተያዘ ከፍተኛ አሉታዊ ውጤት ሊኖረው ይችላል። በፕሮጀክቱ አቅራቢያ ይህንን በአግባቡ የሚያስቀሩ ነገሮች እነደሌሉ ይገመታል።

በግንባታ እና ዕድሳት ሥራዎች የተሰማሩ ተቋራጮች ድምጽ አውጪ የሆኑ ማሽነሪዎችን የሚቆጣጠሩባቸውን ዘዴዎች እና በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገጉትን አማራጭ የግንባታ ሥነ ሥርዓቶች ማወቅ አለባቸው። ወይም ይኸው ከሌለ ዓለም ዓቀፍ ጥሩ አሠራርን መከተል ይኖርባቸዋል።

ዝርዝር፣ ዓይነተኛ የማሽነሪ የድምጽ ኃይል ደረጃዎች በፕሮጀክት ቁጥጥር ላይ ምክር የሚሰጥባቸው እና ድምጽ ቅነሳው ላይ መመሪያ የሚቀመጥባቸው ይሆናል። በግንባታ ጊዜ ሊኖሩ የሚችሉ የድምጽ ምንጮች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

ሀ. ከባድ የግንባታ እና የደን ማሽነሪ፤
ለ. የኃይል መሣሪያዎች እና ኮምፕሬሰሮች፤
ሐ. የማቅረቢያ ተሽከርካሪዎች፤
መ. የመቆፈሪያ ሪጎች እና
ሠ. ፓምፖች

የአፈጻጸም መስፈርቶች

የሚከተሉት የአፈጻጸም መስፈርቶች ለፕሮጀክቱ ግንባታዎች ተቀምጠዋል፡-

ሀ. ከግንባታ እና የኦፕሬሽን ሥራዎች የሚወጡ ድምጾች በማናቸውም ድምጽን በማይፈልጉ ቦታዎች የአካባቢ ሁከትን መፍጠር የለባቸውም።
ለ. ከግንባታ ሥራዎች ጋር ተያይዞ በሁሉም ጊዜያት ድምጽን ለመቀነስ የሚያግዙ እርምጃዎችን መውሰድ፤
ሐ. ከግንባታ እና ኦፕሬሽን ሥራዎች በሚወጡ መርገብገቦች ከሳይቱ ውጪ ያሉ ንብረቶች መጎዳት የለባቸውም።
መ. ቅሬታዎች በቀረቡ በ48 ሰዓት ውስጥ የማስተካከያ ዕርምጃ በመውሰድ ምላሽ መሰጠት አለበት።

ቁጥጥር

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ለፕሮጀክቱ ደረጃውን የጠበቀ የድምጽ መቆጣጠሪያ ፕሮግራም ጎልብቷል። ፕሮግራሙ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ በየሦስት ወሩ የሚከለስ እና የሚሻሻል ይሆናል። የሳይት ተቆጣጣሪው የሚከተሉትን መፈጸም ይጠበቅበታል፡-

ሀ. ማሽነሪዎች እና መሣሪያዎች በመደበኛነት መጠገናቸውን እና በአግባቡ መሥራታቸውን ማረጋገጥ፤ እና

ለ. ድምጽ ለማውጣት አቅም ያላቸውን የግንባታ ሥራዎች በቀን ሰዓታት፣ ማለትም ከጠዋቱ 1፡00 እስከ ቀኑ 11፡30 ብቻ ማከናወን።

ሪፖርት ማድረግ

ሁሉም የድምጽ መከታተያ/መቆጣጠሪያው ውጤቶች/ክስተቶች በሰንጠረዥ የሚቀመጡ እና በእቅዱ እንደተቀመጠው ሪፖርት የሚደረጉ ይሆናሉ። የአካባቢና የደን ሚንስቴር ማናቸውም የሚጠረጠሩ የማቴሪያል ክስተቶች ወይም ከፍተኛ አካባቢን የሚጎዱ ነገሮች በሚከሰቱበት ጊዜ ወይም የአፈር መሸርሸርን እና የዝቅጠት መቆጣጠሪያን በተመለከተ ከተወሰነው ደረጃ ከበለጠ ወዲያውኑ ሊገለጽለት ይገባል።

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ሰንጠረዥ 4፡- የድምጽ እና መርገብገብ መቆጣጠሪያ እርምጃዎች

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
ድ1፡ የጨመረ የድምጽ ደረጃ	ድ. 1.1 ሁሉንም የፓምፕ መሳሪያዎች አካቶ በግንባታ እና በኦፕሬሽን ጊዜ የድምጽ መውጣትን የሚቀንሱ ትክሎችን እና መሳሪያዎችን እና ልዩ የዲዛይን የሥራ ልምዶችን መምረጥ	በሁሉም ምዕራፎች	ተቋራጭ	የመያዣ መዛግብት
	ድ. 1.2 እንደ ሳይለንሰር እና ሙፊር ያሉ ልዩ የድምጽ መቀነሻ መሳሪያዎችን እንዳግባብነቱ መግጠም	በቅድመ ግንባታ እና በግንባታ ጊዜ	ተቋራጭ	የመያዣ መዛግብት
	ድ 1.3 ድምጽ አውጪ/አመንጪ የግንባታ ሥራዎች ከሥራ ሰዓት ውጪ ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 11፡30 የሚከናወኑ ከሆነ የእነዚህኑ ድምጾች አስፈላጊነት ይቀነሱ እና የድምጾቹ መመንጨት/መውጣት ይገደብ	በግንባታ ምዕራፍ	ሁሉም ሰራተኞች	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ድ 1.4 በተለይም ድምጽ አውጪ/አመንጪ የግንባታ ሥራዎች ከሥራ ሰዓት ውጪ ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 11፡30 የሚከናወኑ ከሆነ ከግንባታ እንቅስቃሴዎቹ ቀደም ብሎ አቅራቢያ ያሉትን ነዋሪዎች ማማከር	ግንባታ ምዕራፍ	ሁሉም ሰራተኞች	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ድ 1.5 በሳይቱ ላይ የሚኖሩ ከመጠን በላይ ድምጽ አውጪ/አመንጪ መሳሪዎችን በሌሎች አማራጮች ለመተካት ምትክ የመቆጣጠሪ ስትራቴጂዎችን መጠቀም/መተግበር	ግንባታ ምዕራፍ	ሁሉም ሰራተኞች	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ድ1.6 በተለዩ ነዋሪዎች ተጽዕኖ በሚኖርበት ጊዜ ጠታር/ደረቅ ድምጽ የሚከላከሉ/ሚያፍኑ ጊዜያዊ የግንባታ ድምጽ መከላከያዎችን ማቅረብ	ግንባታ ምዕራፍ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ድ1.7 ሁሉም ከድምጽ ጋር የተያያዙ ቅሬታ የቀረበባቸው እና ያልቀረበባቸው ክስተቶች በሳይት የክስተት ሪፖርት ማድረጊያ ሥነ-ሥረዓቶች መሰረት ሪፖርት ተደርገው በዋና መዝገብ ማጠቃለያቸው ይሰራል	ግንባታ ምዕራፍ	የሳይት ተቆጣጣሪ	የመያዣ መዛግብት
	ድ1.8 ተቋራጩ እርምጃዎችን በመፈጸም በሥራ ክንውኖች ጊዜ ከመጠን በላይ የሆኑ ድምጾችን የመቀነስ አስፈላጊነትን ግንዛቤ ለማሻሻል ለሠራተኞቹ እና ኦፕሬተሮቹ ስልጠና ማካሄድ አለበት	በቅድመ ግንባታ እና በግንባታ ጊዜ	ተቋራጭ	የመያዣ መዛግብት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

እዝል VI (ለ) - የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
ድ1፡ በግንባታ ምክንያት የሚመጣ መርገብገብ	ድ2.1 ከፕሮጀክቱ ግንባታ እና ኦፕሬሽን የተነሳ በመርገብገብ ተጎጂ ሚሆኑ ንብረቶችን፣ መዋቅሮችን እና የመኖሪያ ቦታዎችን መለየት	በቅድመ ግንባታ እና በግንባታ ጊዜ	ተቋራጭ	የመያዣ መዛግብት
	ድ 2.2 ከግንባታ እና ኦፕሬሽን መርገብገብ ተጸዕኖ ለሚከሰቱ የድምጽና የመርገብገብ ጉዳቶች ጊዜዊ እና ቋሚ የመቀነሻ እርምጃዎችን መንደፍ	በቅድመ ግንባታ	ተቋራጭ	የመያዣ መዛግብት
	ድ2.3 ሁሉም ከመርገብገብ ጋር የተያያዙ ቅሬታ የቀረበባቸው እና ያልቀረበባቸው ክስተቶች በሳይት የክስተት ሪፖርት ማድረጊያ ሥነ-ሥረዓቶች መሰረት ሪፖርት ተደርገው በዋና መዝገብ ማጠቃለያቸው ይሰራል	በግንባታ ምዕራፍ	የሳይት ተቆጣጣሪ	የመያዣ መዛግብት
	ድ2.4 በግንባታ ጊዜ የከርሰ ምድር አገልግሎቶችን ከግንባታ እና ኦፕሬሽን መርገብገብ ተጸዕኖ ለመጠበቅ እና ለማራቅ ደረጃቸውን የተበቁ እርምጃዎች ይወሰዳሉ	በግንባታ ምዕራፍ	የሳይት ተቆጣጣሪ	የመያዣ መዛግብት

እዝል VI (ለ) - የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

የአየር ጥራት

ሁሉም የግንባታ፣ የቁፋሮ እና የተሃድሶ ወይም የጥገና የሥራ እንቅስቃሴዎች የአየር ጥራት ሁከት መንስኤ የመሆን የታመቀ ችሎታ አላቸው።

የፕሮጀክቱ አካባቢዎች በባህርያቸው በዋናነት ገጠራማ ወይም የደን አካባቢዎች ናቸው። አሁን ያለው የአየር ጥራት እነዚህን አካባቢዎች የሚያንጸባርቅ ሲሆን በዚህ ውስጥም አቧራ ዋነኛው የአየር ጥራት ብክለት ወይም ሁከት ነው።

በግንባታ እና በክንዋኔ ስራዎች ውስጥ የሚሳተፉ ተቋራጮች የአየር ጥራትን የመቀነስ ተጽዕኖ ያላቸውን ዘዴዎች መቀነሱ ላይ እና በኢትዮጵያ ህግ ወይም በአለም አቀፍ የጥሩ አሰራር ውስጥ ያሉትን አማራጭ የግንባታ አካሄዶች ማወቅ አለባቸው።

የአፈጻጸም መስፈርቶች

የሚከተሉት የአፈጻጸም መስፈርቶች ፕሮጀክቶችን ለመገንባት የተቀመጡ ናቸው፡-
ሀ. የሚለቀቅ አቧራ/ደቃቅ ነገር ለአካባቢ ሁከት/ብክለት መንስኤ መሆን የለበትም፤
ለ. ከግንባታ እና ክንዋኔ የስራ እንቅስቃሴዎች ጋር በተገናኘ የአየር ጥናት አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ ሁል ጊዜም የሚያግዙ እርምጃዎችን ማከናወን፤ እና
ሐ. በ48 ሰዓት ውስጥ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ምላሽ ለመስጠት የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣

ቁጥጥር

ደረጃውን የጠበቀ የአየር መቆጣጠሪያ ለፕሮጀክቶች ጎልብቷል። መርሃ ግብሩ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ በየሁለት ወራቱ የሚከለስ እና የሻሻል ይሆናል። በተለይም የሳይት ተቆጣጣሪው፡-

ሀ. ሁሉም የሚከመሩ ነገሮች አቧራን እንዳያወጡ የተሸፈኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፤ እና
ለ. የአቧራ ማመቂያ መስፈርቶች በሁሉም ሰራተኞች እና በአካባቢና ደን ሚንስቴር እንዲሁም በዩኤንዲፒ ሰራተኞች የየእለት ወይም የተለመዱ የሳይት ፍተሻዎችን በሚያደርጉበት ጊዜ (ዝቅተኛው ድግግሞሽ በሳምንት አንዴ) በእይታ መታየት አለባቸው።

ሪፖርት ማድረግ

ሁሉም የአየር ጥራት መቆጣጠር ውጤቶች እና/ወይም ክስተቶች በዕቅዱ እንደተቀመጠው በሰንጠረዥ ሆነው ሪፖርት መደረግ አለባቸው። የሚጠረጠሩ ማናቸውም የቁሳቁስ ክስተቶችን ወይም ከፍተኛ የአካባቢያዊ ጉዳት የሚያመጡ ነገሮች በሚከሰቱበት ጊዜ ወይም የአየር ጥራትን በተመለከተ የተወሰነው ደረጃ ያለፈ በሚሆንበት ጊዜ ለአካባቢና ደን ሚንስቴር ወዲያውኑ ሊገለጽለት ይገባል።

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

እዝል VI (ለ) - የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

ሰንጠረዥ 5፡- የአየር ጥራት አያያዝ እርምጃዎች

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
ሀ1፡- በአስቸጋሪ ቦታዎች የአቧራ ደረጃዎች መጨመር	ሀ1.1፡- በዲዛይን፣ በግንባታ እና በክንዋኔ/ኦፕሬሽን ጊዜያት በሁሉም ቦታዎች ውጤታማ የአቧራ አያያዝ እርምጃዎችን መፈፀም	በቅድመ ግንባታ እና በግንባታ ጊዜ	ሁሉም ሰራተኞች	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ሀ.1.2፡- ጉልህ የግንባታ መስቀመጫና የማከናቻ ቦታዎች ተብለው በተለዩት ላይ የአቧራ መለኪያ መግጠም	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ሀ.1.3፡- በማናቸውም አስቸጋሪ በሚባሉ ቦታዎች የአካባቢ ብክለት እንዲከሰት የሚያደርጉ ልቀቶች አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ የአቧራ/ደቃቅ ነገሮች የሚያወጡ እንቅስቃሴዎችን መቆጣጠር	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ሀ.1.4፡- የግንባታ እንቅስቃሴዎች ከአየር ንብረት ክስተቶች ጋር የተያያዙ ጉዳቶችን መቀነስ አለባቸው	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ሀ.1.5፡- ዋና ዋና የዕፅዋት ጉዳትን እና የመሬት ስራዎችን ለመቀነስ ለቀረቡ ስራዎች መርሃ ግብርን/ደረጃን መፈፀም	በሙሉ ግንባታ	ተቋራጭ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ሀ.1.6፡- በሳይት ላይ የሚከመሩ ወይም የሚከማቹ ቁሳቁሶች ለስራዎቹ እስከሚያስፈልጉ ድረስ አለመታዘዛቸውን እና/ወይም አለመገዛታቸውን ማረጋገጥ	በሙሉ ግንባታ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ሀ.1.7፡- የቁሳቁሶች ማከማቻ ቦታዎችን እስከሚቻል ድረስ ከአስቸጋሪ ተቀባዮች አርቆ ማስቀመጥ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ሀ.1.8፡- ከማናቸውም የውሃ ገደቦች ጋር በሚጣጣም መልኩ ለአቧራ መቆጣጠር ስራዎች ተስማሚ ጥራት ያለው በቂ ውሃ ምንጮችን ማግኘት	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት

እዝል VI (ለ) - የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት	ቁጥጥር እና ሪፖርት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

			የሚወስደው	የሚደረገው
ሀ1፡- በአስቸጋሪ ቦታዎች የአቧራ ደረጃዎች መጨመር	ሀ1.9፡- የእጽዋት ዝርያዎችንህልውና በከፍተኛ ደረጃ ለማረጋገጥ የማድነን ስራዎችን መርሃ ግብር መፈፀም	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	የመያዣ መዝገብ
	ሀ.1.10፡- የአየር ትራት አያያዝ እቅድ መጎልበቱንና መፈፀሙን ማረጋገጥ	በቅድመ ግንባታ እና በግንባታ ጊዜ	ተቋራጭ	የመያዣ መዝገብ
	ሀ.1.11፡- የቆሻሻ መያዣዎች እና ቆሻሻዎች መሸፈናቸውንና ከአስቸጋሪ ቦታዎች በሚቻል መጠን ርቀት መቀመጣቸውን ማረጋገጥ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	የመያዣ መዝገብ
	ሀ.1.12፡- በመንገዶችና በመዳረሻ መንገዶች ፍጥነቶችን መገደብ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ሀ.1.13፡- የሀውል መኪናዎች፣ መሳሪያዎች እና ትክል/ፕላንት ጥቅም ላይ በማይሆኑበት ጊዜ ጭነታቸውን መሸፈን	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
ሀ2፡- ተሽከርካሪዎች የሚያወጡትን መጨመር (ሽታዎችንና ጭስ አካትቶ)	ሀ.2.1፡- የግንባታ ተሽከርካሪዎች ጥቅም ላይ በማይውሉበት ጊዜ መቆማቸውን/ሞተራቸው መጥፋቱን ማረጋገጥ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ሀ.2.2፡- ስራዎችን ለማከናወን የሚፈለጉ ተሽከርሪዎች ብቻ በሳይቱ ላይ መስራታቸውን ማረጋገጥ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ሀ.2.3፡- ሁሉም የግንባታ ተሽከርካሪዎች፣ ትክል እና ማሽነሪዎች በዲዛይን ደረጃዎችና በልዩ መስፈርቶች መሰረት የተጠገኑና የሚሰሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት

እዝል VI (ለ) - የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
ሀ2፡- ተሽከርካሪዎች የሚያወጡትን መጨመር (ሽታዎችንና ጭስ አካትቶ)	ሀ.2.4፡- ከሳይቱ ጋር በተያያዘ ዝቅተኛውን የአካባቢ አያያዝ መስፈርቶችን ቢያንስ መዘርዘር የሚያካትተውን ለሁሉም የሳይት ሰራተኞች የማስተዋወቂያ መርሃ ግብር አጎልብቶ መፈፀም	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ሀ.2.5፡- የግንባታ መኪና ማቆሚያ እና የተሽከርካሪ/ትክል/መሳሪያ ማከማቻ ቦታዎችን ተግባራዊ እስከሚደረግ ድረስ ከአስቸጋሪ ቦታዎች ማራቅ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ሀ.2.6፡- የተንቀሳቃሽ ትክል/ፕላን የጭስ ማውጫዎችን ከመሬት እንዲርቅ ማድረግ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ሀ.2.7፡- የቆሻሻ መያዣዎች እና ቆሻሻዎች መሸፈናቸውንና ከአስቸጋሪ ቦታዎች በሚቻል መጠን ርቀት መቀመጣቸውን ማረጋገጥ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

የኬሚካልና የነዳጅ አያያዝ

በግንባታ እና የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓዶች በሚቆፈሩበት ጊዜ በሳይት ሊከማቹ የሚችሉት ቁልፍ የኬሚካል እና የነዳጅ ዓይነቶች የሚከተሉትን የሚያካትቱ ሲሆን ነገር ግን በእነዚህ አይገደቡም፡-

ሀ. የትክል መሳሪያዎችን እና ጀነሬተሮችን ለመሙላት ናፍታ እና ቤንዚን

ለ. በግንባታ እና በቁፋሮ ስራዎች ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ ግሪስ ወዘተ‰፤ እና

ሐ. የግብርና ኬሚካሎች

በአግባቡ ካልተያዙ፣ ካልተከማቹ ወይም ጥቅም ላይ ካልዋሉ የመሬት፣ የገጽታ ውሃ እና የከርሰ ምድር ውሃ ስርዓቶች ብክለት ይከሰታል። በግንባታ እና በኦፕሬሽን ስራዎች ጊዜ የጎጂ ማቴሪያሎች መለቀቅ ለተወሰነ ቦታ አካባቢ ከፍተኛ እምቀት ያለው ጉዳትን ያስከትላል። በመሆኑም ሁሉም ዘይቶች፣ ግሪስ፣ ናፍታ፣ ቤንዚን እና ኬሚካሎች በሳይቱ የተወሰነ ቦታ መከማቸት አለባቸው።

ፍሳሽን ለማስከተል አቅም ያላቸው እንቅስቃሴዎች፡-

ሀ. ማሽነሪዎችንና ተሽከርካሪዎችን መጠቀም - ለነዳጆች፣ ዘይቶች እና ቅባቶች መፍሰስ እምቀት ያላቸው፤

ለ. ነዳጆችን፣ የማሽነሪ ዘይቶችን እና ግሪስን ማጓጓዝ፣ ማከማቸት እና አያያዝ፤

ሐ. የሲሚንቶ/አስፋልት (ሬንጅ) እና የሌሎች የግንባታ ቁሳቁሶች ማጓጓዝ፣ ማከማቸትና አያያዝ፤

መ. ለመስኖ እቅድ ወይም ለደን ኦፕሬሽኖች የሚጠቅሙ ማናቸውንም ኬሚካሎች ወደ ከባቢ አካባቢ መልቀቅ መቻል፤

ሠ. ከጎጂ ቁሳቁሶች ጋር የተያያዙ አሉታዊ ተፅዕኖዎች በዋናነት ተያያዥ የሚሆኑት በግንባታ እና በኦፕሬሽን ምዕራፍ ጊዜ ውስጥ ከሚኖረው የማከማቸትና የአያያዝ ሁኔታ ጋር ነው።

የአፈጻጸም መስፈርቶች

የሚከተሉት የአፈጻጸም መስፈርቶች ፕሮጀክቶችን ለመገንባት የተቀመጡ ናቸው፡-

ሀ. የማቴሪያል ደህንነት ዳታ ሰነድ መዝገብ በሳይቱ ላይ ለሚያዙ ሁሉም ኬሚካሎችና ነዳጆች መጎልበቱን ማረጋገጥ፣

ለ. ጎጂ ቁሳቁሶችን አግባብነት ባላቸው ህጎችና በተሻሉ የአያያዝ አሰራሮች መሠረት መያዝ እና ማከማቸት፣

ሐ. ሁሉም ፍሳሾች ለአካባቢና ደን ሚንስቴር በተከሰቱ በ**አንድ ሰዓት** ጊዜ ውስጥ ሪፖርት ማድረግ፤ እና

መ. ማናቸውም ፍሳሾች በዚህ አካባቢ ባሉ የውሃማ አካባቢዎች እንዳይገቡ ማድረግ፣ እና

ሠ. ቁጥጥር የማይደረግባቸውን የዘይት፣ ግሪስ እና ናፍጣ ወደ አካባቢው መለቀቅ መከላከል፣

ረ. ምንም ዓይነት የጎጂ ማቴሪያሎች ፍሳሽ እንዳይኖር ማድረግ፣ ምንም ዓይነት የኬሚካል ፍሳሾች ወደ ከርሰ ምድር የውሃማ አካላት እንዳይገቡ ማድረግ፤ እና

ሰ. በጎጂ ማቴሪያሎች ፍሳሽ የተነሳ የመሬት ብክለት እንዳይኖር ማድረግ

ቁጥጥር

የኬሚካል እና የነዳጅ አያያዝ መርሃ ግብር ለፕሮጀክቶች ጎልብቷል። መርሃ ግብሩ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ በየሁለት ወራቱ የሚከለስ እና የሻሻል ይሆናል። በተለይም የሳይት ተቆጣጣሪው፡-

ሀ. የየዕለት የኬሚካል እና የነዳጅ ቁጥጥሮችን በየእለት የመቆጣጠሪያ ሥነ-ሥርዓት መሠረት ማካሄድ አለበት፤

ለ. ዝቅተኛ የአካባቢ ተፅዕኖን ለማረጋገጥ የኬሚካሎችን አመራረጥ፣ ግዢ፣ ክምችት፣ አያያዝ እና ማስወገድ መቆጣጠር አለበት፣

ሐ. ነዳጅን፣ ቅባቶችን እና/ወይም የሀይድሮሊክ ፈሳሽን የሚጠቀሙ መሳሪያዎችን በቋሚነት መፈተሽ/መመርመር አለበት፤

መ. በፍሳሽ የሚወጡ ወዘተ‰ ቁሳቁሶችን ከብክለት ነጻ የማድረግና የማጽዳት ሂደት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ሁሉንም መሳሪያዎች በቋሚነት መፈተሽ/መመርመር አለበት፤

ሠ. ፍሳሾችን የሚይዙ፣ የሚቀንሱ እና ከጎጂነት ነጻ የሚያደርጉ አሰራሮችን ማጎልበት እና መሳሪያዎችን መትከል

ሪፖርት ማድረግ

የሚጠረጠሩ ማናቸውም የቁሳቁስ ክስተቶችን ወይም ከፍተኛ የአካባቢያዊ ጉዳት የሚያመጡ ነገሮች በሚከሰቱበት ጊዜ ወይም የአየር ጥራትን በተመለከተ የተወሰነው ደረጃ ያለፈ በሚሆንበት ጊዜ ሜፌክ ወዲያውኑ ሊገለጽለት ይገባል።

ሰንጠረዥ 6፡- የኬሚካል እና የነዳጆች አያያዝ እርምጃዎች

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
ኬ 1፡- የኬሚካሎችና የነዳጆች ጥንቃቄ የጎደለው የሆነ አያያዝ	ኬ 1.1፡- ለእምጃዎቹ ምላሽ የሚሰጡ የፍሳሽ አያያዝ እቅድን ማዘጋጀት	የፖስት ድህረ-ግንባታ	ተቋራጭ	የመያዣ መዛግብት እና ሳምንታዊ ሪፖርት
	ኬ 1.2፡- አግባብነት ባላቸው ደረጃዎችና መመሪያዎች ውስጥ እንደተገለፁት ሁሉንም ኬሚካሎች፣ ነዳጆች፣ ዘይቶችና ጉዳት ለማምጣት የታመቀ ችሎታ ላላቸው ቁሳቁሶች ማከማቻን ማዘጋጀትና ማከማቸት፤ ሁሉም ጎጂ ቁሳቁሶች በሳይቱ ላይ ጥቅም ላይ እንዲውሉ መጽደቅ/መፈቀድ አለባቸው። ሁሉም ጎጂ ቁሳቁሶች እና የግንባታ ነዳጅ አግባብነት ባላቸው የማከማቻ አገልግሎት መስጫዎች መከማቸት አለባቸው (ለምሳሌ ነዳጅ/ኬሚካል በተከለለ አካባቢ መከማቸት አለባቸው)	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ኬ 1.3፡- የሀይድሮ ካርበን ዝቃጮች የከለር ምልክት በተሰጣቸው ቦታዎች መከማቸት አለባቸውና ምልክት የተሰጣቸው በርሜሎች በነዳጅ ዲፖዎች አካባቢ መቀመጥ አለባቸው እና በዚሁ መሰረት መወገድ አለባቸው።	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ኬ 1.4፡- የሚቻል በሚሆንበት ጊዜ የነዳጅ እና ኬሚካል ክምችትና አያያዝ በማዕከላዊ የነዳጅ እና የኬሚካል ማከማቻ አገልግሎት መስጫዎች ለምሳሌ የነዳጅ ማደያ/የሳይት ዲፖ መከማቸት አለባቸው።	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ኬ 1.5፡- የነዳጅና የኬሚካሎች በሳይት ላይ የሚረግ ክምችት በዝቅተኛ መጠን መያዝ አለበት።	በግንባታ ጊዜ	ተቋራጭ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ኬ 1.6፡- ለዘይት እና ኬሚካል ፍሳሾች የአስቸኳይ ጊዜ የማጽጃ ሳጥኖች በሳይት እና በሁሉም ትልልቅ ተሽከርካሪዎች መኖር አለባቸው።	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
	ኬ 1.7፡- ነዳጅ እንደገና የመሙላት ስራዎች ከሳይት ውጪ እንዲሆኑ የሚመረጥ ቢሆንም በሳይት ላይ መሙላት ካስፈለገ ይኸው አግባብነት ያላቸው የመከላከያ እርምጃዎች ቀደም ብለው የተዘጋጁ/ቦታ የተለየላቸው ሲሆን በሳይቱ የተለዩ ቦታዎች መደረግ አለበት፤ እና እነዚህ ቦታዎችም ከገጽታ ውሃ እና የማፋሰሻ መስመሮች ከ20ሜ ማነስ የለባቸውም።	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ኬ 1.8፡- ገበሬዎች/የደን ባለሞያዎች የግብርና ኬሚካሎችን መጠቀሙ ላይ በአግባቡ መሰልጠን አለባቸው	የፖስት ድህረ-ግንባታ		የመያዣ መዛግብት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ፕሮጀክቱ የተነደፈው በባለድርሻ አካላት ድጋፍ ሆኖ የሰፊውን ማህበረሰብ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ በማለም ነው። ነገር ግን ግንባታን፣ ቁፋሮን ወይም በመሬት አጠቃቀም ላይ ለውጥ የሚያስከትሉ ማናቸውም ፕሮጀክት ላይ እንዳለው አንዳንድ አለመርካቶች ሊከሰቱ ይችላሉና ግጭቶችም ሊነሱ ይችላሉ። ለውጥረት እምቀት ያላቸው አካባቢዎች ቀደም ብለው መታወቃቸውና ግጭቱን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ አግባብነት ያላቸው እርምጃዎች መወሰዳቸው አስፈላጊ ነው።

ፕሮጀክቱ እና ንዑስ ፕሮጀክቶቹ ፈቃደኛ ያልሆነ መስፈርን እና መሬትን በከፍተኛ ደረጃ መውሰድን አይፈልጉም። ነገር ግን አንዳንድ ንዑስ ፕሮጀክቶች የውሃ ጉድጓዶችን፣ የመስኖ ቦታዎችን፣ የአየር ፀባይ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችን፣ የግል ንብረቶች ላይ መግባትን የሚያስፈልጉ የማከማቻ አገልግሎት መስጫዎችን ለመስቀመጥ መሬትን ሊፈልጉ ይችላሉ። የኢትዮጵያ መንግስት ህጎች እና የጂሲኤፍ የአፈጻጸም ደረጃዎች ካሳን በተመለከተ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ይዘዋል።

ወረዳ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በእያንዳንዳቸው 22 ተሳታፊ ወረዳዎች ስር በወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት የሚቋቋሙና በወረዳው/የመሬት አቀማመጥ ፕሮጀክት አስተባባሪዎች የሚመሩ ይሆናሉ። የወረዳ ፕሮጀክት አስተባባሪዎቹ እለተእለት የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎችን እና ሂደቶችን የሚመሩ ሲሆን ባለድርሻ አካሎችን ያሳትፋሉና ማህበረሰቡን በታለመው የመሬት አቀማመጥ ደረጃ ያንቀሳቅሳሉ። በእያንዳንዱ ወረዳ የቀበሌ/የመንደር ማህበረሰባት በፕሮክት አፈጻጸሙ ላይ የሚሳተፉ ሲሆን ኃላፊነታቸው የሚከተሉትን ያካትታል። ነገር ግን በእነዚህ አይገደብም፣ የተጠቃ መረጣ፣ ማህበረሰብ መዋጮን ማስተባበር እና በፕሮጀክት አስተዳደሩ ማህበረሰቡን መወከል።

የአፈጻጸም መስፈርቶች

የሚከተሉት የአፈጻጸም መስፈርቶች ፕሮጀክቶችን ለመገንባት የተቀመጡ ናቸው፡-

ሀ. ከማህበረሰቡ ጋር ውይይት ተደርጓል እና የፕሮጀክቱ አካላት በእውቀት ላይ በተመሰረተ ምክክራቸው መሠረት የተነደፉ ናቸውና በሙሉ ፕሮጀክት ይሳተፋሉ፤

ለ. ሁሉም ባለድርሻ አካላት በአግባቡ ተወክለዋል፤

ሐ. በግንባታ እና በኦፕሬሽኖች ጊዜ በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ የሚደርሱ ጎጂ ተፅዕኖዎች ይወገዳሉ፤ እና የማይቻል ከሆነ እነዚህ ተፅዕኖዎች መቀነስ፣ ወደነበሩበት መመለስ ወይም ካሳ መስጠት፣

መ. የማህበረሰቡ የመሬት አጠቃቀም ከፍ ይላል እና አነስተኛ ተጨማሪ የመሬት አካባቢዎች ከተፈለጉ እነዚህኑ ማግኘት ድርድር የሚደረግበትና ካሳም የሚሰጥበት ይሆናል።

ሠ. የባህላዊ ትውፊቶች በከፍተኛ ሁኔታ ጉዳት የሚደርስባቸው ወይም ተፅዕኖ የሚመጣባቸው አይሆኑም፣

ረ. የማህበረሰቡ ጤና እና ደህንነት ይጠበቃልና ከፕሮጀክቱ ሁሉን አቀፍ የብልጽግና ጥቅሞች የሚገኙ ይሆናል፣

ሰ. የቅሬታ ማቅረብ ሥነ-ሥርዓቶች የሚቀመጡ እና በአግባቡ የሚያዙ ይሆናሉ፤

ሸ. የረዥም ጊዜ ማህበራዊ ጥቅሞች የሚሳኩ ይሆናል፤

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ሁሉም ባለድርሻ አካላትን የማህበረሰብ አባላት በፕሮጀክት አፈጻጸሙና ቁጥጥሩ ላይ የሚጫወቱት ቁልፍ ሚና አላቸው።

ከባለድርሻ አካሎች ጋር የሚደረጉ ምክክሮች የሚቀጥሉ ይሆናል። ይህ ባለድርሻ አካላት ፕሮጀክቱን፣ የግስጋሴ ሂደቱ እና በፕሮጀክቱ የሚኖሩ ማናቸውንም ለውጦች ማወቅ መቀጠላቸውን ያረጋግጣል። ማናቸውም ጉዳዮች በሚነሱበትን ጊዜ መለየቱ ላይም ያግዛል።

በቀበሌ (ማህበረሰብ) ደረጃዎች የልማት ሰራተኞች ለምክር ድጋፍ እና ለአካባቢው ተጠቃሚዎች (በዋናነት ገበሬዎች) የኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ኃላነት የሚኖርባቸው ይሆናል። የልማት ሰራተኞች የቁሳቁስ ግብዓቶችን ለማከፋፈልና የቴክኒካዊ ስልጠና ለመስጠት እንዲሁም በመርሃ ግብር እንቅስቃሴዎቹ አፈጻጸም ላይ የጀርባ አጥንት ለመሆን ኃላፊነት ይኖርባቸዋል።

ሪፖርት ማድረግ

የሁሉም ምክክሮች መዛግብት የሚመጡ እና በየወሩ ሪፖርት የሚደረግ ይሆናል።

ማናቸውም የግል ወይም የማህበረሰብ ቅሬታዎች ወይም አለመርካት በሚከሰቱበት ጊዜ የአካባቢና ደን ሚንስቴር ሪፖርት ይደረግለታል ወይም እንዲያውቀው ይሆናል፤ እና የቅሬታ መፍቻ ሥነ-ሥርዓቶች የተከበሩ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ሰንጠረዥ 7፡- የማህበረሰብ አያያዝ እርምጃዎች

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
የማ.አ1፡- ወደ ግጭት የሚመሩ የመሬት አጠቃቀም ለውጦች	ማ.አ 1.1፡- የመሬት አጠቃቀም ላይ ለውጦችን የማድረግ ዓላማ እና ጥሞች ላይ ከማህበረሰቡ ጋር ምክክር ማካሄድ	ድህረ-ግንባታ	አካባቢና ደን ሚንስቴር	የመያዣ መዛግብት
	ማ.አ 1.2፡- በመሬት አጠቃቀም ለውጥ ላይ የማህበረሰቡን ፈቃድ ማግኘት	ድህረ-ግንባታ	አካባቢና ደን ሚንስቴር	የመያዣ መዛግብት
	ማ.አ 1.3፡- በገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር (ቁ. 456/2005) መሠረት ያሉትን መስፈርቶች በተጣጣመ ሁኔታ የማህበረሰቡ የመሬት አጠቃቀም ወይም ካሳ መስጠት	ድህረ-ግንባታ	አካባቢና ደን ሚንስቴር	የመያዣ መዛግብት
	ማ.አ 1.4፡- ፕሮጀክቱ በሚፈፀምባቸው የተመረጡ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ህገ-ደንቡን በተግባር ላይ ከማዋል በፊት ህገ-ደንብንና የቅድመ ፍተሻን ማዘጋጀት	ድህረ-ግንባታ	አካባቢና ደን ሚንስቴር	የመያዣ መዛግብት
	ማ.አ 1.5፡- የቅሬታ ማስተናገጃ ሂደት መመለሻ መኖሩን ማረጋገጥ፣	በሙሉ ፕሮጀክት	አካባቢና ደን ሚንስቴር	የመያዣ መዛግብት
የማ.አ 2፡- የረዥም ጊዜ ከጥቅም መጋራት ጋር የተያያዘ ግጭትን መፍታት	ማ.አ 2.1፡- በማህበረሰብ ምክክር የዓላማና የጥቅም መጋራት ላይ የምክክር ክንውን ማካሄድ	ድህረ-ግንባታ	አካባቢና ደን ሚንስቴር	የመያዣ መዛግብት
	ማ.አ 2.2፡- በማህበረሰቡ የሚመራ እና በባለቤትነት የተያዘ መተዳደሪያ ደንብ ማጎልበት እና ይህም በግልጽ ከዚህ ማህበረሰብ የማህበረሰብ መሬት ተጠቃሚነት እንዲሁም በማህበረሰቡ የተረጋገጡትን ድንጋጌዎች ማጎልበት፤	ድህረ-ግንባታ	አካባቢና ደን ሚንስቴር	የመያዣ መዛግብት
	ማ.አ 2.3፡- ቅሬታ የቀረበበትን ሁኔታ ሚፈታበትን ሂደት ማረጋገጥ	በሙሉ ፕሮጀክት	አካባቢና ደን ሚንስቴር	የመያዣ መዛግብት
የማ.አ 3፡- የውሃ ምደባ ግጭት	ማ.አ 3.1፡-በውሃ አቅርቦት ስርዓት፣ ዓላማ እና አስተዳደር/አያያዝ ላይ የማህበረሰብ ምክክርን ማካሄድ	ድህረ-ግንባታ	አካባቢና ደን ሚንስቴር	የመያዣ መዛግብት
	ማ.አ 3.2፡- ስምምነት ላይ በተደረሰበት የውሃ ማከፋፈል ድንጋጌዎች ላይ የውሃ አቅርቦት ሥርዓትን ማጎልበት	ድህረ-ግንባታ	አካባቢና ደን ሚንስቴር	የመያዣ መዛግብት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
የማ.አ 3፡- የውሃ ምደባ ግጭት	ማ.አ 3.3፡- ቅሬታዎች የሚፈቱበትን ሂደቶች መጠቀማቸውን ማረጋገጥ	በሙሉ ፕሮጀክት	አካባቢና ደን ሚንስቴር	የመያዣ መዛግብት
የማ.አ 4፡- በህዝብ/መንግስት ሁከት ትቅም ላይ የዋሉ ግንባታ/ክንዋኔ እንቅስቃሴዎች (ለምሳሌ ድምጽ፣ አቧራ ወዘተ‰)	ማ.አ 4.1፡- እንቅስቃሴዎቹን ከማከናወን ቀደም ብሎ የማህበረሰብ ምክክርን ማካሄድ	ድህረ-ግንባታ	አካባቢና ደን ሚንስቴር	የመያዣ መዛግብት
	ማ.አ 4.2፡- አግባብነት ያላቸው የአስተዳደር/አያያዝ እቅዶችን መፈፀም (እባክዎ ድምጽ፣ አየር፣ ስኬፕ፣ ከዕቅዱ፣ የተመረጡ ቆሻሻዎች)	ተቋራጭና አሞፕሬሽን	የሳይት ተቆጣጣሪ እና የአካባቢና ደን ሚንስቴር	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ማ.አ 4.3፡- ቅሬታዎች የሚፈቱበትን ሂደቶች መጠቀማቸውን ማረጋገጥ	ሁሉም ምዕራፎች	አካባቢና ደን ሚንስቴር	የመያዣ መዛግብት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

የቆሻሻ አያያዝ

የአካባቢና ደን ሚንስቴር የቆሻሻ አያያዝ/አወጋገድ ተግባርን ይደግፋል። የሚመረጠው የቆሻሻ አያያዝ ቅደም ተከተልና መርሃ ግብሮች የሚፈለጉትን ጥሩ የቆሻሻ አወጋገድ/አያያዝ መርሆዎች ለመያዝ የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ. የቆሻሻ አወጋገድ (በፕሮጀክቶቹ ላይ አላስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎችን በማስወገድ መጠቀም)

ለ. ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል (ቁሳቁሶቹን እንደገና መጠቀም እና ማስወገድን መቀነስ)

ሐ. ቆሻሻን መልሶ መጠቀም (እንደ ቆርቆሮዎች፣ የላስቲክ ማሸጊያዎች ወዘተ‰ ያሉትን፤ እና

መ. የቆሻሻ አወጋገድ (ሁሉም የተበከሉ ቆሻሻዎች በተፈቀደላቸው የመሬት ቦታዎች መጣል አለባቸው)

በግንባታ ጊዜ የሚፈጠሩ ቁልፍ የቆሻሻ ፍሰቶች የዝቃጭ ክምችቶችን እና የሚከተሉትን የግንባታ ዝቃጮችን ሊይዝ ይችላል፡-

ሀ. በመሬት ጠረጋ ስራ ጊዜ እንደገና ለመጠቀም ተስማሚ ያልሆኑ ተቆፍረው የወጡ ቁሳቁሶችን ማስወገድ

ለ. ከግንባታ እና ቁፋሮ መሳሪያዎች ጥገና የሚወጡ ዝቃጮች የተለያዩ ከባድ ተሽከርካሪዎችና የተሽከርካሪ መሳሪያዎች በግንባታው እና በቁፋሮው ምዕራፎቹ የጊዜ ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ ይሆናል። ይህንን መሳሪያ ከማጽዳት፣ ከመጠገን እና ከማደስ የሚወጡ አደገኛ የፍሳሽ ቆሻሻዎች ሊከሰቱ ይችላሉ። በተመሳሳይ መልኩ በሳይቱ ውስጥ የሚኖሩ የነዳጆች፣ ዘይቶች፣ ፍሳሾች በአግባቡ መወገድ አለባቸው።

ሐ. የሰራተኞች አገልግሎት መስጫዎች ለምሳሌ መፀዳጃ ቤቶችን በመጠቀም አደገኛ ያልሆኑ የፍሳሽ ቆሻሻዎች ሊወጡ ይችላሉ።

መ. አጠቃላይ ቆሻሻዎች ቁርጥራጭ ማቴሪያሎችን እና የባዮ ብስባሽ ቆሻሻዎችን ያካትታሉ። በግንባታ እና ኦፕሬሽናል የስራ እንቅስቃሴዎች የሚሳተፉ ተቋራጮች በስራዎቹ መሠረታዊ የሆኑ አሻራዎችን ለመቀነስ እና የተጎዱ አካባቢዎችን ወደነበሩበት እንዲመጡ ለማድረግ እጽዋትን የመመንጠር ተጽዕኖዎቹን የሚቀነስባቸውን ዘዴዎች ማወቅ አለባቸው። እነዚህን ስራዎች በመስራት ፕሮጀክቶቹ ከፕሮጀክቱ የሚወጡ የቆሻሻ ተፅዕኖዎችን መቀነስ አለባቸው።

የአፈጻጸም መስፈርቶች

የሚከተሉት የአፈጻጸም መስፈርቶች ፕሮጀክቶችን ለመገንባት የተቀመጡ ናቸው፡-

ሀ. የቆሻሻ አወጋገድ ሰንሰለትን (ማስወገድ፣ መቀነስ፣ እንደገና መጠቀም) በመፈፀም የሚወጡ ቆሻሻዎችን መቀነስ

ለ. በፕሮጀክቱ ኮሊደር ወይም አካባቢዎች በሳይቱ ሰራተኞች የስራ እንቅስቃሴ የተነሳ ምንም ዓይነት ሊትር መታየት የለበትም።

ሐ. የቆሻሻ መውጣትን እና አያያዝን በተመለከተ ምንም ዓይነት ቅሬታዎች መቅረብ የለባቸውም።

መ. ተንቀሳቃሽ ካልሆኑ የንጽህና መጠበቂያ አገልግሎቶች የሚወጡ ማናቸውም ቆሻሻዎች የቆሻሻ ማስወገድ ፈቃድባለው ተቋራጭ ከሳይቱ መወገድ አለባቸው።

ሠ. ከዘይት መለያ የሚገኙ የቆሸሹ ዘይቶች መሰብሰብ እና ከሳይቱ መወገድ አለባቸው ወይም ሪሳይክል መደረግ አለባቸው፤ ለአገር ውስጥ የዘይት ኩባንያዎች ወይም እንደገና ለሚጠቀሙት መጫን አለባቸው።

ለፕሮጀክቶቹ የቆሻሻ አወጋገድ ቁጥጥር መርሃ ግብር መቆልበት አለበት። መርሃ ግብሩ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ በየሁለት ወሩ መከለስ እና መሻሻል አለበት።

ሪፖርት ማድረግ

ማናቸውም በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያመጡ የማቴሪያል ሁኔታዎች በሚጠረጠሩበት ጊዜ ወይም ቆሻሻው ከተወሰነ ደረጃ በላይ ማለፉ ከተወሰነ የአካባቢና ደን ሚንስቴር ወዲያውኑ ሪፖርት ይደረግላታል ወይም ሊነገረው ይገባል።

ሰንጠረዥ 8፡- የቆሻሻ አወጋገድ እርምጃዎች

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
ቆ.አ1፡- ቆሻሻ ማመንጨት እና ሀብትን በከፍተኛ ሁኔታ መጠቀም	ቆ.አ 1.1፡- ቀጥታ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ቆሻሻ ማመንጨትን የሚቀንሱ ማቴሪያሎች/ቁሳቁሶች ፕሮጀክቱን ለመገንባት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።	ድህረ-ግንባታ	የሳይት ተቆጣጣሪ	የመያዣ መዛግብት
	ቆ.አ 1.2፡- ለውጫዊ የቆሻሻ አስወጋጅ አካላት ስራዎቹ ካልተሰጡ በስተቀር የየእለት የቆሻሻ ማስወገድ ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል።	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ቆ.አ 1.3፡- የግንባታ ቁሳቁሶችን መጠቀም ከፍ ይደረጋል እና የሚቻል ከሆነ እንደገና የመጠቀም ፖሊሲ ጥቅም ላይ የውላል።	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በሳምንታዊ እና የመያዣ መዛግብት
	ቆ.አ 1.4፡- የተናጠል የቆሻሻ ማስወገጃ ሁኔታዎች በሁሉም ጊዜያት ይያዛሉ። ማለትም አጠቃላይ የቤት ቆሻሻ፣ የግንባታ እና የቁፋሮ ቆሻሻ እና የብክለት ቆሻሻ። በሳይቱ የሚኖሩ የተለዩ አካባቢዎች የተለያዩ ቆሻሻዎችን በጊዜያዊነት ለማስወገጃ ይቀመጣሉ። ለእያንዳንዳቸው የቆሻሻ ማስወገጃዎች በቂ ምልክት እና ቀለም ያላቸው የኮድ ቢኖች የሚሰጣቸው ይሆናል።	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በሳምንታዊ እና የመያዣ መዛግብት
	ቆ.አ 1.5፡- ማናቸውም የተበከሉ ቆሻሻዎች በተፈቀደ የመሬት መድፊያ ላይ የሚወገዱ ይሆናል።	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በሳምንታዊ እና የመያዣ መዛግብት
	ቆ.አ 1.6፡- ተመልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉ ቆሻሻዎች (ዘይትን እና የተወሰኑ የግንባታ ቆሻሻዎችን አካትቶ) በተናጠል የሚሰበሰቡና በትክክል የሚወገዱ ይሆናል።	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ቆ.አ 1.7፡- የቆሻሻ ማስወገጃ ሳይቶች የዱር እንስሳት አለመጉዳታቸውን በማረጋገጥ በየእለቱ በበቂ ሁኔታ መሸፈን አለባቸው	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ
የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው
ቆ.አ 1፡- ቆሻሻ ማመንጨት እና ሀብትን በከፍተኛ ሁኔታ መጠቀም	ቆ.አ 1.8፡- ሁሉንም ማጣሪያዎች አካትቶ የቆሻሻ መወገድ በኢትዮጵያ መንግስት መስፈርቶች መሰረት ይከናወናል።	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በሳምንታዊ እና የመያዣ መዛግብት
	ቆ.አ 1.9፡- የመቆፈሪያ ሪጎችን አካትቶ ከተሽከርካሪዎች እና ትክል የሚወጡ የነዳጅ እና የቅባት ፍሳሾች ወዲያውኑ መወገድ አለበት።	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ቆ.አ 1.10፡- ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ዋና ዋና የጥገና እና የእድሳት ስራዎች ከሳይቱ ውጪ ይደረጋሉ።	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በሳምንታዊ እና የመያዣ መዛግብት
	ቆ.አ 1.11፡- የዛፎች መወገድ ከሚከተሉት ዘዴዎች በአንደኛው ወይም ከዚያ በላይ በሆኑት ይፈፀማል፡- ሀ. በቦታው ይተዋሉ ለ. መቁረጥ እና መፍጨት እና ትልቅ የቅርንጫፍ ክፍሎች ለንግድ እንጨት መፍጫ/መሰንጠቂያ ሊሸጡ፣ ሊተላለፉ ይችላሉ።	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በሳምንታዊ እና የመያዣ መዛግብት
	ቆ.አ 1.12፡- የሀይድሮ ካርበን ቆሻሻዎች በነዳጅ ዲፖዎች አካባቢ በሚኖሩ ባለቀለም ኮዶች እና ምልክት የተሰጣቸው በርሜሎች መከማቸት አለባቸው	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ቆ.አ 1.13፡- በሚቻልበት ጊዜ ሁሉ የነዳጅ እና የኬሚካል ማከማቻ እና አያያዝ በማዕከላዊ የነዳጅ እና የኬሚካል ማከማቻ አገልግሎት መስጫዎች ለምሳሌ እንደ ነዳጅ ጣቢያዎች የሚደረግ ይሆናል።	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት

ጉዳዩ	የመቆጣጠር ተግባር (እና ምንጭ)	የድርጊቱ ጊዜ	ኃላፊነት የሚወስደው	ቁጥጥር እና ሪፖርት የሚደረገው

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ቆ.አ 1፡- ቆሻሻ ማመንጨት እና ሀብትን በከፍተኛ ሁኔታ መጠቀም	ቆ.አ 1.14፡- በሳይት ላይ የሚደረጉ የነዳጅ እና የኬሚካል ክምችቶች በዝቅተኛ መጠን ይሆናሉ።	በግንባታ ጊዜ	ተቋራጭ	በየእለቱ፣ የመያዣ መዛግብት እና ማናቸውንም ክስተቶች ሪፖርት ማድረግ
	ቆ.አ 1.15፡- ማናቸውም የዘይቶችና የቅባቶች ቆሻሻዎች በሚቻል መጠን ተሰብስበው እንደገና ለሚጠቀሙ ወይም በተመደበላቸው የማስወገጃ ሳይቶች ይጓጓዛሉ	በግንባታ ጊዜ	የሳይት ተቆጣጣሪ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት
	ቆ.አ 1.16፡- በሳይት ላይ የተከማቹ ማናቸውም አደገኛ እቃዎች በኢትዮጵያ ደንቦች መሠረት የሚከማቹ ይሆናሉ።	በግንባታ ጊዜ	ተቋራጭ	በየእለቱ እና የመያዣ መዛግብት

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

እዝል 1፡- በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ክለሳ መነሻነት በውሃ እና ኢነርጂ ዘርፍ የፕሮጀክት መፈፀምን ማጽደቅ ወይም አለማጽደቅን በተመለከተ በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ስልጣንን በውክልና መስጠት[5]

አንቀጽ 1
የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ኃላፊነቶች

1. የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር በዚህ ሰነድ ላይ አባሪ በተደረጉት ዝርዝሮች መሰረት የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የአዲስ የልማት ፕሮጀክቶችን ወይም ባሉት ፕሮጀክቶች ላይ የሚደረጉ ከፍተኛ ማስፋፊያዎችን ወይም ለውጦችን ወይም የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን እንደገና ማልማትን ተጽዕኖዎች መመርመር አለበት እና ከቅድመ ሁኔታዎች ጋር ወይም ያለቅድመ ሁኔታዎች ማጽደቅ ወይም መከልከል አለበት እና የፕሮጀክቱን አፈጻጸም መቆጣጠር አለበት።
2. የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የፕሮጀክቱ አካላት ከሚኒስቴሩ ወይም ከፌዴራል ወይም ከክልሎች የአካባቢያዊ ኤጀንሲዎች ማናቸውም ሰራተኞች እንዳልተሳተፉ ማረጋገጥ አለበት እና ሚኒስቴሪ ከእነዚሁ አካላት የተፈረመ ምስክር መጠየቅ አለበት፤
3. የአካባቢያዊ ጥበቃ ባለስልጣን ሪፖርት ከቀረበ በኋላ በጣም ከፍተኛ ቀደም ብለው ያልታዩ ጉዳዮች በሚኖሩበት ጊዜ ሁሉ የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ እንዲደረግ ወይም እንዲከለስ ወይም ዳግም እንዲሰራ መጠየቅ አለበት እና ይህም ሚኒስቴሪ አዲሱን ሁኔታ እንዲመረመረው ለማስቻል ነው።
4. የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ቢያንስ በየሶስት ወደልማት ፕሮጀክቶቹ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነዶችን ቅጂ ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ማቅረብ አለበት። የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የአካባቢ ክፍሉ በውክልና የተሰጠው ስልጣን ለመፈጸም በቂ ችሎታ እንዳለው ማረጋገጥ አለበት
5. በዚህ በውክልና በተሰጠ ስልጣን ያሉ ተግባራትን ለማጠናቀቅ የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እንደአስፈላጊነቱ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ 2
የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ኃላፊነቶች

1. የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተጽዕኖ ጥናቶችን እንዲያካሂድ ለማስቻል የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ክለሳ እና የተሰጡ ውሳኔዎችን በተመለከተ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ህጎችን፣ ደረጃዎችን እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን አዘጋጅቶ ያቀርባል።
2. የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የአካባቢ ክፍል ሰራተኞች የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ክለሳዎች ላይ ስልጠና እና የአቅም ግንባታ ይሰጣል።
3. በውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተሰጡ ውሳኔዎችን የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በሚከልስበት ጊዜ የአካባቢ ተጽዕኖ ዳሰሳ ሰነድ ስህተት ከሆነ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ስህተቱን የማስተካከል መብት አለው።
4. የፕሮጀክቱ ገምጋሚ በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ላይ በውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ውሳኔ ካልረካ ይኸው ገምጋሚ አለመርካቱን መጀመሪያ ላይ ለውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ባለስልጣናት ያሳውቃል እና ጉዳዩ ካልተፈታ ገምጋሚው ጉዳዩን ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ያቀርባል። የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የገምጋሚውን የጽሑፍ ቅሬታ ከተቀበለ በኋላ በ15 ቀናት ውስጥ ለውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና ለገምጋሚው ውሳኔውን ይሰጣል።

---

[5] □□□ □□□□ □□□□□ □□ □□□□□ □□□□□ □□□□ □ 2013 □.□.□

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

5. የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ይህንን በውክልና የተሰጠ ስልጣን መፈፀምን ከፍ ለማድረግ እርምዎችን ሊወስድ ይችላል።
6. የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በውክልና በተሰጠው ስልጣን ጋር ተያይዘው ያሉ የልማት ፕሮጀክቶችን ዝርዝሮች ሊያሻሽል ይችላል።

ይህ በውክልና የተሰጠ ስልጣን በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እና በውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የሚፀና ይሆናል።

_____ _____

የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር

በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 መሠረት በውሃ እና ኢነርጂ ሴክተር ስር ያሉ የፕሮጀክቶች ዝርዝር፤

1. የግድብ ግንባታ
   ሀ. ከ15ሜ በላይ ከፍታ ያላቸው ግድቦች
   ለ. መጠኑ ከ3 ሚሊዮን ሜትር ኩብ በላይ የሆነ ማከማቻ
   ሐ. ከ10 ሜጋ ዋት በላይ የሆነ የሀይድሮ ፓወር
2. የመስኖ ግንባታ - ከ300 ሄክታር በላይ
3. የፔትሮሊየም እና የኃይል/ኢነርጂ ዘርፍ ፕሮጀክቶች
4. ከ25,000 ሊትር እና ከዚያ በላይ የማከማቻ ታንከሮች
5. ለአካባቢ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎች በ300 ሜ ውስጥ ያሉ ማናቸውም የውሃ እና የኢነርጂ ፕሮጀክቶች

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ
የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

አርማ	አርማ
የማህበራዊና የአካባቢያዊ ግምገማ ክፍል	የተ.መ.ል.ፕ

ለማህበራዊና አካባቢያዊ ግምገማ ክፍል ጥያቄ የማቅረቢያ መመሪያ እና/ወይም የባለድርሻ አካላት ምላሽ አሰራር

<u>የዚህ ፎርም ዓላማ</u>

- **ይህንን ፎርም የሚጠቀሙ ከሆነ እባክዎ መልስዎትን ጽሑፉን ለመለጠት በደመቀ ጽሑፍ ያቅርቡ**
- **ይህንን ፎርም መጠቀም የሚመከር ቢሆንም የግድ የሚያስፈልገን አይደለም። ጥያቄውን በሚረቅበት ጊዜ እንደመመሪያ ሊያገለግል ይችላል።**

ይህ ፎርም የሚከተሉትን እንዲያግዝ የታሰበ ነው፡-

(1) የተ.መ.ል.ፕ የማህበራዊ ወይም የአካባቢያዊ ፖሊሲዎቹን ወይም ግዴታዎቹን እያከበረ አይደለም ብለው በማመን እና በዚሁም የተነሳ እየተጎዱ መሆንዎን ካመኑ ጥያቄው ይቀርባል። ይህ ጥያቄ በተ.መ.ል.ፕ የቁጥጥር እና ምርመራዎች ጽ/ቤት ውስጥ ባለው በማህበራዊና አካባቢያዊ ግምገማ ክፍል፣ ገለልተኛ ምርመራ የሚያከናውነው የቅሬታ ግምገማ ሊጀመር የሚችል ሲሆን ይህም የሚደረገው የተ.መ.ል.ፕ ፖሊሲዎች ወይም ግዴታዎች መጣሳቸውን ለመወሰን እና እነዚህን ጥሰቶች ለማስተካከል እርምጃዎችን ለመለየት ነው። የማህበራዊ እና አካባቢያዊ ግምገማ ክፍል የሁኔታውን ፍሬ ነገር ለመወሰን በቅሬታ ግምገማው ጊዜ ከእናንተ ጋር የሚሰራ ይሆናል። የቅሬታ ግምገማውን ውጤቶች መረጃ እንዲያውቁት ይደረጋል።

እና/ወይም

(2) የተ.መ.ል.ፕ ፕሮጀክቶች በእናንተ ላይ ከፍተኛ የማህበራዊ ወይም የአካባቢ ተጽዕኖ እያላቸው እንደሆኑ ወይም ሊኖራቸው እንደሚችል በሚያምኑበት ጊዜ የተ.መ.ል.ፕ ባለድርሻ አካላት ምላሽ ጥያቄን በማቅረብ የተጎዱ ማህበረሰቦችን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን (የመንግስት ተወካዮች፣ የተ.መ.ል.ፕ ወዘተ.) አንድ ላይ ለማምጣት ሂደቱን መጀመርም ትችላላችሁ። ይህ የባለድርሻ አካላት ሂደት በተ.መ.ል.ፕ የኢትዮጵያ ጽ/ቤት ይመራል ወይም በተ.መ.ል.ፕ ዋና መ/ቤቶች ሊመቻች ይችላል። የተ.መ.ል.ፕ ሰራተኞች እውነታውን ለመፈለግ እና ለልማት መፍትሄዎች የምላሹ አካል በመሆን ከእናንተ ጋር ይነጋገራሉና ይሰራሉ። ሌላ የፕሮጀክት ባለድርሻ አካላቶች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሊሳተፉ ይችላሉ።

ከመንግስት ተወካዮች ወይም ለፕሮጀክቱ ኃላፊ ከሆኑት የተ.መ.ል.ፕ ሰራተኞች ጋር በቀጥታ በመገናኘት የሚያሳስባችሁን ነገር ለመፍታት ጥረት ያላደረጋችሁ ከሆነ እባካችሁ የተ.መ.ል.ፕ የባለድርሻ አካላት ምላሽ ሥነ-ሥርዓት ይህንኑ ጥረት ጥያቄውን ከማቅረባችሁ በፊት እንድታደርጉት እንዲስተዋል ይሁን።

ሚስጥራዊነት የቅሬታ ግምገማ ሂደቱን የሚመርጡ ከሆነ ማንነትዎን በሚስጥር መያዝ ይችላሉ (ማንንትዎን ለቅሬታ ግምገማ ቡድን ብቻ ይታወቃል) የባለድርሻ አካል ምላሽ ሥነ-ሥርዓትን

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

ከመረጡ በመጀመሪያው የመቻል ማጣሪያ እና የጉዳያችሁ ግምገማ ጊዜ ውስጥ ማንነታቸውን በሚስጥር ለመያዝ መምረጥ ትችላላችሁ። ጥያቄያችሁ ተገቢ ከሆነና ግምገማውም ምላሽ መሰጠቱ አግባብነት እንዳለው ካመላከተ የተ.መ.ል.ፕ ሰራተኞች የቀረቡትን ምላሾች ከእናንተ ጋር ይወያዩበታልና የማንነታችሁን ሚስጥራዊነት እንዴት መያዝ እንዳለበት ይወያያሉ።

መመሪያ

ጥያቄ በምታቀርቡበት ጊዜ እባካችሁ በሚቻል መጠን ብዙ መረጃዎችን እንድታቀርቡ ይሁን። ያልተሟላ ፎርም በስህተት በኢሜይል ከላኩ ወይም መስጠት ሚፈልጓቸው ተጨማሪ መረጃዎች ካላችሁ የመከታተያ ኢሜይል ማናቸውንም ለውጦች በማብራራት በቀላሉ መላክ ትችላላችሁ።

ስለእርስዎ መረጃ

እርስዎ ‰

1. የተ.መ.ል.ፕ በሚረዳቸው ፕሮፕጀክቶች የተጎዱ ሰው ነዎትን?
   በእርስዎ ላይ ተፈጻሚነት ባለው መልስ ቀጥሎ Xj የሚለውን ምልክት ያድርጉ
   አዎ አይደለሁም

2. የተጎዱ ሰዎች ወይም ቡድኖች ስልጣን ያለው ተወካይ ነዎትን?
   በእርስዎ ላይ ተፈጻሚነት ባለው መልስ ቀጥሎ Xj የሚለውን ምልክት ያድርጉ
   አዎ አይደለሁም

ስልጣን የተሰጠው ተወካይ ከሆኑ የምትወክሏቸውን ሁሉንም ሰዎች ስሞችና ስለእነርሱ ሆነው እንዲሰሩ የተሰጠዎትን የውክልና ስልጣን ሰነድ <u>አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ፋይሎችን ከዚህ ፎርም ጋር አባሪ በማድረግ</u> እንዲሰጡ ይሁን።

3. የመጀመሪያ ስም፡-
4. የመጨረሻ ስም፡-
5. ሌላ ማናቸውም የመለያ መረጃዎች፡-
6. የመልዕክት አድራሻ፡-
7. የኢሜይል አድራሻ፡-
8. የስልክ ቁጥር (ከሀገር ኮድ ጋር)፡-
9. የእርስዎ አድራሻ፡-
10. የቅርብ ከተማ
11. ማናቸውም ተጨማሪ እርስዎ የሚገኙበት መመሪያዎች
12. ሀገር

ከየተ.መ.ል.ፕ የሚፈልጉት ምንድን ነው፡- የቅሬታ ግምገማ እና/ወይም የባለድርሻ አካል ምላሽ

አራት ምርጫዎች አሎዎት፡-

- ለቅሬታ ግምገማ ጥያቄ ማቅረብ፤
- ለባለድርሻ አካል ምላሽ ጥያቄ ማቅረብ
- ለሁለቱም የቅሬታ ግምገማ እና የባለድርሻ አካል ምላሽ ጥያቄ ማቅረብ
- ለቅሬታ ግምገማ ወይም የባለድርሻ አካል ምላሽ ጥያቄ ማቅረብ እንዳለብዎት እርግጠኛ ካልሆኑ እና ሁለቱም አካላት ጉዳዮችዎን እንዲከልሱ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎን ይህንኑ ይግለጹ።

13. የተ.መ.ል.ፕ ማህበራዊ እና/ወይም አካባቢያዊ ፖሊሲውን ወይም ግዴታውን መወጣት ባለመቻሉ የተ.መ.ል.ፕ በእርስዎ ወይም በማህበረሰብዎ ጉዳት እያደረሰ ነው ወይም ጉዳት ያደርስብናል የሚል ስጋት አለዎትን?
    በእርስዎ ላይ ተፈጻሚነት ባለው መልስ ቀጥሎ Xj የሚለውን ምልክት ያድርጉ
    አዎ አይደለሁም
14. በቅሬታ ግምገማው ሂደት ሁሉ ስምዎ (ስማችሁ) በሚስጥር እንዲያዝ ይፈልጋሉን?
    በእርስዎ ላይ ተፈጻሚነት ባለው መልስ ቀጥሎ Xj የሚለውን ምልክት ያድርጉ
    አዎ አልፈልግም
    በሚስጥር መያዙ ከተጠየቀ እባክዎ ምክንያቱን ይግለጹ፡-
15. ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለምሳሌ መንግስት የተ.መ.ል.ፕ ወዘተ. የተ.መ.ል.ፕ ፕሮጀክት ምክንያት የማህበራዊ ወይም የአካባቢያዊ ተጽዕኖዎችን ወይም ስጋቶችን ብለው የሚያምኗቸውን በጋራ ለመፍታት መስራት ይፈልጋሉን?
    በእርስዎ ላይ ተፈጻሚነት ባለው መልስ ቀጥሎ Xj የሚለውን ምልክት ያድርጉ
    አዎ አልፈልግም
16. ለምላሽ ላቀረቡት ጥያቄ የመጀመሪያ ግምገማ ወቅት ስምዎ (ስማችሁ) በሚስጥር እንዲያዝ ይፈልጋሉን?
    በእርስዎ ላይ ተፈጻሚነት ባለው መልስ ቀጥሎ Xj የሚለውን ምልክት ያድርጉ
    አዎ አልፈልግም
    በሚስጥር መያዙ ከተጠየቀ እባክዎ ምክንያቱን ይግለጹለ፡-
17. ጥያቄዎ የተ.መ.ል.ፕ ዋና መ/ቤቶች እንዲመለሱ ካላመለከቱ በስተቀር ለባለድርሻ አካል ምላሽ የሚቀርቧቸው ጥያቄዎችዎ በተ.መ.ል.ፕ የኢትዮጵያ ቢሮዎች የሚያዙ ይሆናል። የተ.መ.ል.ፕ ዋና መ/ቤቶች ጥያቄዎችዎን እንዲመልሱ ይፈልጋሉን?
    በእርስዎ ላይ ተፈጻሚነት ባለው መልስ ቀጥሎ Xj የሚለውን ምልክት ያድርጉ አዎ
    አልፈልግም
    አዎ ብለው ካመላከቱ እባክዎ ጥያቄው በተ.መ.ል.ፕ ዋና መ/ቤቶች እንዲያዙ የጠየቁበትን ምክንያት ያሳዩ።
18. ሁለቱንም የቅሬታ ግምገማ እና የባለድርሻ አካል ምላሽ ይፈልጋሉን?
    በእርስዎ ላይ ተፈጻሚነት ባለው መልስ ቀጥሎ Xj የሚለውን ምልክት ያድርጉ አዎ
    አልፈልግም
19. ከሁለቱ የቅሬታ ግምገማን ወይም የባለድርሻ አካል ምላሽ የትኛውን መጠየቅ እንዳለብዎት <u>እርግጠኛ አይደሉምን</u>?
    በእርስዎ ላይ ተፈጻሚነት ባለው መልስ ቀጥሎ Xj የሚለውን ምልክት ያድርጉ አዎ አይ

እርስዎን የሚያሳስብዎት የተ.መ.ል.ፕ ፕሮጀክት መረጃዎች እና የሚሳስብዎት ነገር ባህርይ፡-

20. እርስዎን የሚያሳስብዎት የትኛው በተ.መ.ል.ፕ የሚደገፍ ፕሮጀክት ነው (ከታወቀ)
21. የፕሮጀክቱ ስም (ከታወቀ)
22. እባክዎ ስለ ፕሮጀክቱ እርስዎ የሚያሳስብዎትን አጭር መግለጫ ይስጡ
    የተ.መ.ል.ፕ ፕሮጀክት የማህበራዊ ወይም አካባቢያዊ ፖሊሲዎቹን ወይም ግዴታዎቹን ባለማክበሩ የሚያሳስብዎት ከሆነ እዚህን ፖሊሲዎችና ግዴታዎች መለየት ይችላሉ፤ እባክዎ ይለዩ (የግድ አስፈላጊ ግን አይደለም)። እባክዎ በዚሁ የተነሳ የተከሰቱ ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ የማህበራዊ እና አካባቢያዊ ተጽዕኖዎችን ዓይነት ይግለጹ። ተጨማሪ ቦታ ካስፈለገ ማናቸውንም ሰነዶች እባክዎ እንዲያያይዙ ይሁን። በሚመርጡት ማንኛውም ቋንቋ መጻፍ ይችላሉ።

የአካባቢ እና ማህበራዊ አያያዝ እቅድ

የአረንጓዴ የአየር ንብረት የገንዘብ አቅርቦት ሃሳብ/ፕሮፖዛል

23. ስለዚህ ፕሮጀክት የሚያሳስብዎትን ነገር ከመንግስት ተወካዮች እና ስለ ፕሮጀክቱ ኃላፊነት ካለባቸው የተ.መ.ል.ፕ ሰራተኞች ጋር ተወያይተዋልን? መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችስ ጋር?
    በእርስዎ ላይ ተፈጻሚነት ባለው መልስ ቀጥሎ Xj የሚለውን ምልክት ያድርጉ አዎ አይ
    መልሱ አዎ ከሆነ እባክዎ የሚያሳስብዎትን ነገር የተወያዩባቸውን ሰዎች ስም/ሞች ይስጡ።
    ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ያነጋገሯቸው ባለስልጣናት ስም ዝርዝር

የመጀመሪያ ስም	የመጨረሻ ስም	ማዕረግ/ተባባሪነት	የተገናኙበት ቀን ግምት	ከግለሰቡ የተገኘ ምላሽ

24. በፕሮጀክቱ በከፍተኛ ሁኔታ የተጎዱ ሌሎች ግለሰቦች ወይም ቡድኖች አሉን?
    በእርስዎ ላይ ተፈጻሚነት ባለው መልስ ቀጥሎ Xj የሚለውን ምልክት ያድርጉ አዎ የሉም
25. እባክዎ ጥያቄውን የሚደግፉ ሌሎች ግለሰቦችን ወይም ቡድኖችን ስም ዝርዝር እና/ወይም መግለጫ ይስጡ?

የመጀመሪያ ስም	የመጨረሻ ስም	ማዕረግ/ተባባሪነት	የመገኛ መረጃ

ለማህበራዊና አካባቢያዊ ግምገማ እና/ወይም ኤስ አር ኤም
የላኳቸውን ማናቸውንም ሰነዶች በኢሜልዊ ያያይዙ ሁሉም ሰነዶችዎ በአንድ ኢሜይል መላክ የማይችሉ ከሆነ እባክዎ ብዙ ኢሜይሎችን ለመላክ ነጻነት ይሰማዎት።

ማስገባትና ድጋፍ

ጥያቄውን ለማስገባት ወይም ድጋፍ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎ በproject.concerns@undp.org ኢሜይል ያድርጉ።